# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


## የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት እና የጋዜጠኝነት የኮምኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት ፍተሻ


በ

ስዩም ይሁኔ


ሰኔ 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት እና የጋዜጠኝነት የኮምኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት ፍተሻ

በ

ስዩም ይሁኔ

ሰኔ 2012 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| --------------------------------------- | ---------------------------- |

| የፈታኞች ስም | ፊርማ |
|---|---|
| --------------------------------------- | ---------------------------- |
| ------------------------------------------ | -------------------------------- |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን ጥናትና ምርምር ለማድረግ እውቀቱን፣ ኃይሉን እና ብርታቱን የሰጠኝ የሁሉ ፈጣሪ ልዑል እግዚአብሔር በእኔ አንደበት ብቻ ሳይሆን በፈጠረው ስነፍጥረት ሁሉ የተከበረና የተመሰገነ ይሁን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ውድ ጊዜያቸውን መስዋእት በማድረግ ደከመኝና ሰለቸኝ ሳይሉ አባታዊ የሆነ ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠት እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለፐ/ር ጌታሁን አማረ ምስጋናዬ ገደብ የለውም፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ይህን ጥናት ሳደርግ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህሮቼ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ የስርአተትምህርት እና የፈተናዎች ዝግጅት ክፍል ባለሙያዎች እንዲሁም ጓደኞቼ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በመጨረሻም በስራዬ ሁሉ ከጎኔ ለማትለየኝ፣ ለምትደግፈኝ እና ለምታበረታታኝ ለውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ ብርሃን ገበየሁ ያለኝ ክብርና አድናቆት እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

# ማውጫ

አርእስት ገጽ

ምስጋና ------------------------------------------------------------------------------------------- i

ማውጫ ------------------------------------------------------------------------------------------- ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ---------------------------------------------------------------------------- v

አጠቃሎ ------------------------------------------------------------------------------------------ vi

ምእራፍ አንድ

መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------------------------- 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------------------------------------------------------------------------- 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት --------------------------------------------------------------- 5

1.3 የጥናቱ አላማ ---------------------------------------------------------------------------- 6

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ------------------------------------------------------------------- 6

1.5 የጥናቱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------- 7

ምእራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት ---------------------------------------------------------------------------------- 8

2.1 የፈተና ምንነት ------------------------------------------------------------------------- 8

2.2 የቋንቋ ፈተና ምንነት ----------------------------------------------------------------- 9

2.2.1 የቋንቋ ፈተና አላማ ---------------------------------------------------------- 10

2.2.2 የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታ ------------------------------------------------------------ 11

2.2.3 የፈተና አይነቶች ------------------------------------------------------------------ 13

2.2.4 የጥሩ ፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ----------------------------------------------- 16

2.2.5 የቋንቋ ትምህርት እና የቋንቋ ፈተና ተዛምዶ -------------------------------- 19

2.2.6 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ------------------------------------------------- 21

2.2.7 የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች አቀራረብ መርህ ---------------------------------- 23

2.3 የሀገር ውስጥ የቀደሙ ጥናቶች ዳሰሳ ----------------------------------------------- 25

ምእራፍ ሶስት

የአጠናን ዘዴ -------------------------------------------------------------------------------- 28

3.1 የጥናቱ ንድፍ ------------------------------------------------------------------------- 28

3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች ---------------------------------------------------------------- 28

3.3 የናሙና አመራረጥ ------------------------------------------------------------------ 29

3.3.1 የፈተናዎች ናሙና አመራረጥ ------------------------------------------------ 29

3.3.2 የክልልና የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ------------------------------------ 29

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ---------------------------------------------------- 30

3.3.1 የሰነድ ፍተሻ ------------------------------------------------------------------- 30

3.3.2 ቃለ መጠይቅ -------------------------------------------------------------------- 31

3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ---------------------------------------------------------------- 31

ምእራፍ አራት

የመረጃ ትንተና ------------------------------------------------------------------------------------ 34

4.1 የተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ አጭር ቅኝት --------------------------------------- 34

4.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ------------- 36

4.3 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪ ፈተናዎቹ ውስጥ ------------------------- 39

4.4 የመማሪያ መጻህፍቱ እና የሰዋስው ጥያቄዎቹ የይዘት ዝምድና ------------------- 41

4.5 ከምርጫ ጥያቄዎች አቀራረብ መርህ አንጻር የተተኳሪ ጥያቄዎች አቀራረብ ------ 48

ምእራፍ አምስት

ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች ------------------------------------------------------------- 58

5.1 ማጠቃለያ --------------------------------------------------------------------------------- 58

5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች ----------------------------------------------------------------------- 60

ዋቢዎች ---------------------------------------------------------------------------------------------- 62

አባሪዎች

አባሪ አንድ

አባሪ ሁለት

አባሪ ሶስት

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፦ በመማሪያ መጻህፍቱ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶችን የድግግሞሽ መጠን

የሚያሳይ -------------------------------------------------------------------------- 37

ሰንጠረዥ 2፦ በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት የሚያሳይ ------ 40

ሰንጠረዥ 3፦ በ2010 ዓ.ም. በተሰጠውክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎችና

የመማሪያ መጻህፍቱ ዝምድናን የሚያሳይ -------------------------------------- 43

ሰንጠረዥ 4፦ በ2011 ዓ.ም. በተሰጠውክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎችና

የመማሪያ መጻህፍቱ ዝምድናን የሚያሳይ -------------------------------------- 45

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህም ጥናት ቅይጥ የምርምር ዘዴ (አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች) ተስማሚ ሆነው በመገኘታቸው ተመራጭ ሆነዋል፡፡ የናሙና አመራረጥ ሂደቱም ተተኳሪው ክልል እና የክፍል ደረጃ በአላማ ተኮር አመራረጥ ዘዴ ክልላዊ ፈተናዎቹ ደግሞ በጠቅላይ የአመራረጥ ዘዴ ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ የሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ፣ የተተኳሪ ጥያቄዎችን የይዘት ዝምድና በተመለከተ የተገኙ መረጃዎችን በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር በማስላት ወደመቶኛ ተቀይረው ሲቀርቡ የጥያቄዎችን አቀራረብ በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በቁጥርና በመቶኛ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከትንተነው በኋላ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በሁለቱም ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ያላቸው ዝምድና ከፍተኛ እና አዎንታዊ ነው፡፡ ይኸውም በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ያላቸው የይዘት ዝምድና 44.9 በመቶ ሲሆን በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ያላቸው የይዘት ዝምድና ደግሞ 59.3 በመቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከሽፋን አንጻር ሲታዩ ደግሞ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሰፊ ሽፋን ከተሰጣቸው ይዘቶች የተወሰኑ ጥያቄዎች የወጣባቸው ሲሆን፣ ትንሽ ሽፋን ከተሰጣቸው ይዘቶች ደግሞ ብዙ ጥያቄዎች እንዲወጣባቸው ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ይዘቶቹ በፈተናዎቹ ውስጥ የተሰጣቸው ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ ተገቢነት የላቸውም፡፡ የጥያቄዎቹም አቀራረብ ከምርጫ ሰጪ ጥያቄ አቀራረብ መርህዎች አንጻር ሲታዩ በ2010 ዓ.ም እና በ2011 ዓ.ም በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ ከተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል እንደቅደም ተከተላቸው 61.5 በመቶ እና 50 በመቶ የሚሆኑት የአቀራረብ ችግር ያለባቸው ሲሆን፤ 38.5 በመቶ እና 50 በመቶ የሚሆኑት ጥያቄዎች ደግሞ በአንጻራዊነት የምርጫ ሰጪ ጥያቄ የአቀራረብ መርህዎችን ተከትለው የቀረቡ እንደሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አጥኚው የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ በቀጣይ የሚዘጋጁ ክልላዊ ፈተናዎች ከእስካሁኖቹ በተሻለ ሁኔታ መሰረት በአደረጃቸው መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር ዝምድና ያላቸው፤ ይዘቶቹ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በተሰጣቸው ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ መሰረት በፈተናዎቹ ውስጥ ሽፋን እንዲያገኙ እና ጥያቄዎቹ የምርጫ ጥያቄዎች በመሆናቸው ሲዘጋጁ የምርጫ ጥያቄ አቀራረብ መርሆችን መሰረት ባደረገ መልኩ ቢሆን የተሻሉ ፈተናዎችን ማዘጋጀት እንደሚቻል አጥኚው ያምናል፡፡

# ምእራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት መቼ እንደተጀመረ የሚያመለክት እርግጠኛ መረጃ ባይገኝም ለብዙ ዘመናት ልክ እንደሌሎች የትምህርት አይነቶች ሁሉ መርሃ ትምህርት ተዘጋጅቶለት በሁሉም የትምህርት እርከኖች እየተሰጠ መቆየቱንና አሁንም እየተሰጠ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ፈተናዎች ይዘውት እንደተነሱት አላማ የሚለያዩ ቢሆንም የአንድን ቋንቋ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎችን እውቀት ለመለካት ሲባል በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ተማሪዎች ይሰጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ካለ ፈተናም ሊኖር ግድ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

የቋንቋ ትምህርት እና ፈተና ግንኙነትን በተመለከተ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ለአብነት ያህል Brown (1994) የቋንቋ ትምህርት እና ፈተና እርስ በርስ የሚደጋገፉ እና የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው በማለት ሲገልጹ፣ Harrison (1983) ደግሞ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከሚካሄዱ ዋና ዋና ክንውኖች መካከል አንዱ እና የተለያዩ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያስችል መሳሪያ በመሆኑ ከመማር ማስተማሩ ሂደት ነጥሎ ማየት አይቻልም በማለት የሁለቱ ዝምድና ጥብቅ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የሰዋስው ጥያቄዎች የተካተቱባቸው ክልላዊ ፈተናዎች አንድ ለትምህርት የቀረበ የትምህርት ይዘት ከተጠናቀቀ በኋላ ለተማሪዎች የሚሰጡ በመሆናቸው የችሎታ መለኪያ (የማጠቃለያ) ፈተናዎች ይባላሉ፡፡ የእነዚህን አይነት ፈተናዎች ምንነት Alderson et al. (1995) ሲገልጹ አንድን ለደረጃው የቀረበን መርሃ ትምህርት እና መማሪያ መጽሀፍ መሰረት አድርገው የሚዘጋጁና ከትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚሰጡ ናቸው፡፡

መሰረታዊ አላማቸውም ተማሪዎች ወደቀጣዩ የክፍል ደረጃ እንዲዘዋወሩ እንዲሁም ባሉበት እንዲቆዩ (እንዲደግሙ) ለማድረግ የሚያስችል ውሳኔ መስጠት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ስለሆነም የቋንቋ ፈተናዎች የታሰበላቸውን  አላማ እንዲያሳኩ በተገቢው መንገድ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን አስመልክተው Alderson et al. (1995) ፈተናዎች ሲዘጋጁ የተመሰረቱበትን የደረጃ መርሃ ትምህርት ወይም መማሪያ መጽሀፍ መሰረት ማድረግ እንዳለባቸው ሲገልጹ፤ Gronlund (1981) ደግሞ አንድ ፈተና የታሰበውን አላማ ከግብ እንዲያደርስ እና ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጥ ከተፈለገ ተገቢነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ተገቢነት በተለያየ መልኩ የሚገለጽ ቢሆንም በዋናነት ግን አንድ ፈተና በጥያቄነት ያካተታቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በአይነትም ሆነ በመጠን በመርሃ ትምህርቱ ወይም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ሲታይ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚያመለክት ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

ከመርሃ ትምህርቱ ወይም ከመማሪያ መጽሀፉ ይዘት ጋር የጠበቀ ዝምድና ያላቸውንም ፈተናዎች ለማዘጋጀት የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Tabel of Specification) መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሰንጠረዥ በመርሃ ትምህርቱ የተነደፉትን የትምህርት አላማዎች እና ተማሪዎች የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች የያዘ ባለሁለት ረድፍ ቻርት በመሆኑ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱ ወይም ከመማሪያ መጽሀፉ ጋር ያላቸውን የይዘት ዝምድና የሚያጠናክር ነው (ዳንኤል 2006)፡፡

ፈተናዎች በመርሃ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ወካይ ከመሆናቸው በተጨማሪ በአቀራረባቸውም ተገቢነት ያላቸው እና የፈተና አቀራረብ መርሆችን መሰረት ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የፈተና ማቅረቢያ ስልቶች በርካታ ሲሆኑ ለአብነት ያህል ቃላዊ፣ ድርሰታዊ፣ አጭር ጽሁፍ፣ ምርጫ ሰጪ የመሳሰሉት እንደሚጠቀሱ ተስፋዬ (1981፣124) ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ጥያቄዎች በምርጫ መልክ የሚቀርቡ በመሆናቸው በምርጫ ሰጪ የአቀራረብ ስልት ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል፡፡ የምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልት በውስጡ ምርጫ፣ አዛምድ፣ እውነት ወይም ሀሰት፣ የተሰጡትን አማራጮች መሰረት በማድረግ ስህተትን ማረም፣ ክፍት ቦታን መሙላት፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና አረፍተ ነገሮችን ማስተካከል እና የመሳሰሉትን የሚያካትት በመሆኑ

በአንድ ጊዜ በርካታ የትምህርት ይዘቶችን ለመመዘን ያስችላል (Heaton 1975፣ Kitao and Kitao 1996፣ Fulcher and Davidson 2007)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የችሎታ (የማጠቃለያ) ፈተናዎች በአንድ መርሃ ትምህርት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ የቀረበን የትምህርት ይዘት የደረጃው ተማሪዎች ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ የሚሰጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ አንድን ውሳኔ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ግብአቶች መሆናቸውን ነው፡፡ ፈተናዎችም የታለመላቸውን ግብ እንዲመቱ እና አላማቸውን እንዲያሳኩ ከተፈለገ ከመርሃ ትምህርቱ ወይም ከመማሪያ መጽሀፉ ጋር ዝምድና ያላቸው፣ ተገቢ የሆኑ የአቀራረብ መርሆችን የተከተሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችም ሲዘጋጁ የክፍል ደረጃውን መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት መሰረት ያደረጉና ተመጣጣኝ ውክልና ያላቸው እንዲሁም የፈተና አቀራረብ መርሆችን የተከተሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

Madson (1983) በተገቢው መንገድ የተዘጋጁ ፈተናዎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት ጠቀሜታቸው የጎላ ሲሆን፤ በአንጻሩ በተገቢው መንገድ ያልተዘጋጁ ፈተናዎች ደግሞ የሚያስገኙት መረጃ የተዛባ ስለሚሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም በተለያዩ ፈተናዎች ላይ ጥናቶችን በማካሄድ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይቶ ጠንካራ ጎኖች ቀጣይነት እንዲኖራቸው፤ ደካማ ጎኖቹ ደግሞ ወደፊት በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ዳግም እንዳይከሰቱ በማድረግ የመማር ማስተማሩ ሂደት አዎንታዊ ገጽታ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን አስመልክተው Gronlund (1988፣8) አንድን ፈተና በተገቢው መንገድ በመገምገም የትምህርት አላማዎችን ተገቢነት፣ የመርሃ ትምህርቶችን እና የመማሪያ መጻህፍቱን አዘገጃጀት እንዲሁም የማስተማሪያ ዘዴዎችን አጠቃቀም ማሻሻል እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡

ሙሉጻህይ (2005)ም በበኩላቸው Tyler (1969፣121-125)ን ጠቅሰው እንደገለጹት በፈተናዎች ላይ የሚደረጉ ጥናቶች ወይም ግምገማዎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት እና ለፈተና አዘገጃጀት ስልቶች መሻሻል ጠቃሚ መረጃዎችን በመስጠት በኩል ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ ከሚናዎቻቸውም መካከል በመርሃ ትምህርቱ የተቀረጹትን ወይም የተነደፉትን የትምህርት አላማዎች፣ የይዘቶች ተተግባሪነት እና ተገቢነት ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ፤ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን

ጠንካራና ደካማ ጎን ለማሳወቅ፤ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት ማስተካከያዎች እንዲደረጉ ጥቆማ መስጠት የሚሉት ይጠቀሳሉ ።

ስለሆነም በተለያዩ ጊዜያት በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ጥናትና ምርምር ማድረጉ በመርሃ ትምህርቶች እና በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ በቀረቡ የትምህርት ይዘቶች እንዲሁም በማስተማሪያ ዘዴዎች አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን ከማስገኘቱ በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት በሚሰጡ ፈተናዎቹ ላይ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይቶ ጠንካራ ጎኖቹ እንዲጠናከሩ፤ ደካማ ጎኖቹ ደግሞ የሚሻሻሉበትን መንገድ በመጠቆም ወደፊት ተተግባሪነት፣ አስተማማኝ፣ ተገቢነት እና ተገቢ የሆነ አቀራረብ ያላቸው የፈተና ጥያቄዎች እንዲዘጋጁ ለማድረግ ያስችላል፡፡

የዚህ ጥናት አድራጊም ይህን እና ሌሎች መሰል ሀሳቦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት ለመፈተሽ ተነሳስቷል፡፡ በዚህም ምክንያት አጥኚው በፈተና ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶችን ለመዳሰስ ባደረገው ሙከራ በተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች እንዳሉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ለአብነት ያህል አበበች (2004)፣ መሰረት (2005)፣ ሙሉጸሀይ (2005)፣ የትምወርቅ (2007) እና ኤልሳቤጥ (2009) ያካሄዷቸውን የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከእነዚህም ጥናቶች መካከል ከዚህ ጥናት ርእስ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያላቸውን ጥናት ለማየት ብንሞክር አበበች (2004) ከ1998 እስከ 2003 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው በቀረቡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ዝምድና የገመገሙ ሲሆን፤ መሰረት (2005) ደግሞ ከ1999 እስከ 2004 ዓ.ም. በትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በተሰጡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ዝምድና እና አቀራረብ ምን እንደሚመስል ፈትሸዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ጥናቶች በክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ላይ በማተኮራቸው የሚመሳሰሉ ቢሆንም መሰረት (2005) ከ1999 እስከ 2004 ዓ.ም. በትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ በተዘጋጁት እና አበበች (2004) ደግሞ ከ1998 እስከ 2003 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በተሰጡት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናዎች ላይ ያተኮሩ በመሆኑ ልዩነት አላቸው፡፡ ይህም ጥናት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርና ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ላይ በማተኮሩ ከሌሎች ይለያል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው በዚህ የጥናት ርእስ ለማጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች ሁለት ሲሆኑ፣ የመጀመሪያው ምክንያት የቋንቋ ፈተና ዋና አላማ የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት እውቀት መፈተሽ እና ትምህርቱን በተመለከተ የሚያስፈልጉ እንዲሁም ለውሳኔ የሚያበቁ የተለያዩ መረጃዎችን ማስገኘት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ፈተናዎቹ የታለመላቸውን አላማ ከግብ ማድረስ ይችሉ ዘንድ በፈተናዎቹ ውስጥ የሚካተቱ ጥያቄዎች በጥንቃቄ ሊዘጋጁና ብቃታቸውም በየጊዜው ሊፈተሽ ስለሚገባ፤

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ አጥኚው ከአሁን ቀደም በአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን ለመዳሰስ ባደረገው ሙከራ በተለያዩ ክልሎች በተሰጡ ክልላዊ ፈተናዎች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች እንዳሉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው በተተኳሪው ክልል ትምህርት ቢሮ በተለይም በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተዘጋጁት ክልላዊ ፈተናዎች ላይ ምንም አይነት የተካሄደ ጥናት ባለማግኘቱ በክልሉ በተዘጋጁት ክልላዊ ፈተናዎች ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ እና ምን ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሏቸው ማወቁ ጠቀሜታው የጎላ ሊሆን እንደሚችል በመረዳት ለናሙናነት የተመረጡትን የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት እና የአቀራረብ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ተነሳስቷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ሲሆን፤ ከዋናው አላማ የመነጩ የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎችም አሉት፡፡

- በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ተተኳሪ መርሃ ትምህርቶቹን እና መማሪያ መጻህፍቱን መሰረት ያደረጉ መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ፤
- ተተኳሪ የሰዋስው ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቶቹ እና በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሽፋን ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን አለመሆናቸውን መፈተሽ፤
- በተተኳሪ ክልላዊ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ ከምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች አቀራረብ መርህ አንጻር መገምገም፤

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

የቋንቋ ፈተና ለቋንቋ ትምህርት መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ሁሉ በቋንቋ እና በቋንቋ ፈተናዎች ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶችም ለቋንቋ ትምህርት መሻሻል፣ መዳበርና ውጤታማ መሆን የበኩላቸውን ድርሻ ያበረክታሉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ውጤትም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- የክልላዊ ፈተናዎችን አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት በመፈተሽ የሚታዩባቸውን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት ወደፊት ለሚዘጋጁ ክልላዊ ፈተናዎች የሚመለከታቸው አካላት (የክልሉ ትምህርት ቢሮ የስርአተ ትምህርት እና የፈተና ዝግጅት ክፍል ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ የመሳሰሉት) ትኩረት እንዲያደርጉባቸው ጥቆማ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- በክልላዊ ፈተናዎቹ ላይ ለሚታዩ ችግሮች የመፍትሄ ሀሳቦችን ያመላክታል፡፡

- ወደፊት በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ በሰፊው ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ አካላት እንደመነሻ ሀሳብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

በአሁኑ ጊዜ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና በተለያዩ ክልሎች እየተዘጋጀ እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የእነዚህን ክልላዊ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት፣ የአቀራረብ ሁኔታ፣ አስተማማኝነት፣ ተተግባሪነት እና በመሳሰሉት ላይ ጥናትና ምርምር ማድረጉ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አጥኚው ካለበት የጊዜና የጉልበት ውስንነት አንጻር ይህ ጥናት በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት ብቻ ፈትሿል፡፡

በመሆኑም በተተኳሪ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት ሌሎች የትምህርት ይዘቶች ማለትም የቋንቋ ክሂሎችን፣ የስነጽሁፍ እውቀት ዘርፎችን፣የመሳሰልትን በሚመለከት የወጡ ጥያቄዎች እንዲሁም የፈተናዎቹ አስተማማኝነት እና ተተግባሪነት የዚህ ጥናት ትኩረት አይደሉም፡፡

# ምእራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምእራፍ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው እና ጥናቱን ለማካሄድ መሰረታዊ የሆኑ ርእሰ ጉዳዮች ለጥናቱ አመቺ በሆነ መልኩ ተቀናጅተው ቀርበዋል። በመሆኑም ምእራፉ ከዚህ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ንድፈ ሀሳቦችና የቀደምት ጥናቶችን ዳሰሳ አካትቷል። ንድፈ ሀሳቦቹም ስለፈተና አጠቃላይ ግንዛቤ እና ስለቋንቋ ትምህርት ፈተና ምንነት፣ አላማ፣ ጠቀሜታ፣ አይነት፣ ባህርያት፣ የቋንቋ ትምህርትና የፈተና ተዛምዶ እንዲሁም ስለምርጫ ሰጪ ጥያቄ አቀራረብ መርሆች የተለያዩ የመስኩ ምሁራን የሰጧቸውን ገለጻዎች ከጥናቱ ጋር እንዲስማሙ በማድረግ ተብራርተው ቀርበውበታል። በዚህ ምእራፍ ስር የተካተቱት ርእሰ ጉዳዮች ፈተናን የተመለከቱ በመሆናቸው ቀደም ብለው በተጠቀሱት ቀደምት ጥናቶች ውስጥ ከቀረቡት ርእሰ ጉዳዮች ጋር ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ይችላል። ይሁን እንጂ በቀረቡት አንዳንድ ዋቢዎች፣ በሀሳብ አገላለጽ እና አደረጃጀት ልዩነት አላቸው።

## 2.1 የፈተና ምንነት

ፈተና ሰዎች ስለአንድ ነገር ያላቸውን እውቀትና ችሎታ ለመፈተሽ እንዲሁም ፍላጎታቸውንና ዝንባሌዎቻቸውን ለማወቅ የሚረዳ ነው። ስለሆነም ፈተና ማለት የተወሰኑ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የተማሪዎችን ወይም የተፈታኞችን እውቀት፣ ችሎታ፣ የባህሪ ሁኔታና ለውጥ አስመልክቶ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል መሳሪያ ነው (Bachman 1990፣ ያለው 2009)።

Harrison (1983)ም በበኩላቸው በአንድ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከሚካሄዱ ዋና ዋና ክንውኖች መካከል አንዱ የሆነው ፈተና በትምህርት አለም ውስጥ ቀጣይነት ያለው እና ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚረዱ የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል መሳሪያ ስለሆነ ፈተናን ከመማር ማስተማር ሂደት ነጥሎ ማየት እንደማይቻል ይገልጻሉ።

Alderson et al.(1995) እንደሚገልጹት ፈተናዎች እንደሚሰጡበት አላማ እና እንደሚፈለገው የመረጃ አይነት የተለያዩ ናቸው። ለምሳሌ በትምህርት መርሃ ግብር (በትምህርት መስክ)

ውስጥ የሚሰጡ ፈተናዎች በሌሎች መስክ ከሚሰጡ ፈተናዎች ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ። ምክንያቱም ፈተናዎች ለአንድ ትምህርት ጥራት፣ መሳካትና ውጤታማነት ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ከመማር ማስተማሩ ሂደት ተነጥለው የማይታዩ፣ በየትምህርቱ መካከልና መጨረሻ ላይ እየተደጋገሙ የሚሰጡ ናቸው። በሌሎች መስክ የሚሰጡትን ፈተናዎች ስናይ ግን ቀጣይነት የሌላቸው እና ከአንድ ጊዜ በላይ የማይደገሙ ናቸው። ለማስረጃነት ያህል በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ሰራተኞችን አወዳድሮ ለመቅጠር የሚሰጡ ፈተናዎች ለተፈለገው አላማ ከዋሉ በኋላ አይደገሙም።

በአጠቃላይ ፈተናዎች የአሰጣጣቸው አይነትና ደረጃ የሚለያይ ቢሆንም በትምህርት ሙያ ውስጥም ሆነ ከትምህርት ሙያ ውጪ በሆኑ የስራ መስኮች ተግባራዊ የሚሆኑ እና ውሳኔዎችን ለመስጠት እንደ መረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩት ማብራሪያዎች አጠቃላይ የፈተናን ጽንሰ ሀሳብ መሰረት ያደረጉ ናቸው። ይሁን እንጂ የዚህ ጥናት ትኩረት በአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ቀጥሎ የቋንቋ ትምህርት ፈተና ምንነትን፣ አላማን፣ ጠቀሜታን እና አይነቶችን አንድ በአንድ ለማየት እንሞክራለን።

## 2.2 የቋንቋ ፈተና ምንነት

በአንድ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች ይሰጣሉ። ከእነዚህ የትምህርት አይነቶች መካከል አንዱ የቋንቋ ትምህርት ነው። ስለሆነም በአንድ የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ክሂሎች፣ የስነጽሁፍና የስነልሳን የእውቀት ዘርፎች፣ የመሳሰሉት ንኡሳን ርእሰ ጉዳዮች ይካተታሉ። እነዚህም ንኡሳን ርእሰ ጉዳዮች ከታሰበው አላማና ግብ መድረስ አለመድረሳቸውን እንዲሁም ተማሪዎች ከትምህርቱ በደረጃቸው የሚጠበቅባቸውን እውቀት መገብየታቸውን ለመረዳት የቋንቋ ፈተና አስፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል። ይህንን አስመልክተው Weir (2005) የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች ከተማሩት የቋንቋ ትምህርት ወይም ይዘት መካከል ምን ያህሉን እንደተረዱትና የቋንቋ ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያሳይ መሆኑን ያብራራሉ።

Bachman (1990)ም በበኩላቸው የችሎታ መለኪያ ፈተናን በመጥቀስ የችሎታ መለኪያ ፈተና ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ክሂሎችና በእውቀት ዘርፎች ላይ ሲሆን ዋና አላማውም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ መመዘን እንደሆነ ያስረዳሉ። ምሁሩ አክለውም የቋንቋ ፈተና በተወሰነ ጊዜ ለተወሰነ አላማ ለተማሪዎች የሚቀርብን ትምህርት መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን ተናጠላዊ ችሎታ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን (የቋንቋ ክሂሎችን፣ የሰዋስውና የስነጽሁፍ የእውቀት ዘርፎችን) በተናጠልም ይሁን በቅንጅት በማቅረብ ተማሪዎች ምን ያህል እንዳዳበሯቸው ለመፈተሽ ከማገልገላቸው በተጨማሪ የተለያዩ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የሚረዱ ዋና መሳሪያዎች ናቸው ማለት ይቻላል። በዚህም ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ፈተናዎች ተፈታኝ ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መዘዋወር መቻል አለመቻላቸውን ውሳኔ ለመስጠትና ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ናቸው።

### 2.2.1 የቋንቋ ፈተና አላማ

የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች ለተለያዩ አላማዎች ይዘጋጃሉ። ይህንን አስመልክተው ተስፋዬ (1981) ከቋንቋ ትምህርት ፈተና አላማዎች መካከል የተማሪዎችን ቅድመ ችሎታ ለማወቅ፣ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ያላቸውን የእውቀትና የችሎታ ደረጃ ለመገምገም፣ የተማሪዎችን ጥንካሬና ድክመት ለመለየት፣ የመሳሰሉት እንደሆኑ ይገልጻሉ። ይህ የሚያሳየው ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች የሚዘጋጁት ተማሪዎች ከትምህርት በፊትና በኋላ ያላቸውን እውቀት (ችሎታ) ለመለካት መሆኑን ነው።

Heaton (1975)ም በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ፈተና አላማ እንደሚዘጋጁበት ጉዳይ የሚለያዩ መሆናቸውን ገልጸው ለማስረጃነትም የክፍል ውስጥ (ተከታታይ) ፈተናዎች እና የማጠቃለያ ፈተናዎች አላማ የተለያየ ነው። ምክንያቱም የክፍል ውስጥ ፈተናዎች አላማ መምህራን የተማሪዎችን የፈተና ውጤት መነሻ በማድረግ የማስተማሪያ ስልታቸውን የሚቀይሩበት፣ የሚያሻሽሉበትና የሚያጎለብቱበት፣ ተማሪዎች የትኞቹን የትምህርት ይዘቶች

በደንብ እንደተረዷቸው እና እንዳልተረዷቸው በመለየት ድክመታቸውን ለማሻሻል ነው፡፡ የማጠቃለያ ፈተናዎች አላማ ደግሞ የትኞቹ ተማሪዎች የተሻለ ብቃት እንዳላቸው መለየት፣ መገምገም፣ መምረጥ፣ ማወዳደር እና ውሳኔ መስጠት ነው ይላሉ፡፡ ይህም ጥናት ትኩረት ያደረገባቸው ጥያቄዎች ማጠቃለያ በሆኑ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙ በመሆናቸው ተፈታኝ ተማሪዎች ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ መዘዋወር መቻል አለመቻላቸውን ለመወሰን የሚያስችሉ ናቸው፡፡

### 2.2.2 የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታ

የቋንቋ ትምህርት ፈተና በአንድ የትምህርት መስክ ውስጥ ከትምህርት አሰጣጥ ዝግጅት እስከ ክፍል ውስጥ ትግበራ ድረስ ያለውን አስፈላጊ መረጃ ለመስጠት የሚያገለግል ነው፡፡ ጥንቃቄና ትኩረት በተሞላበት መልክ የሚዘጋጁ ፈተናዎች ትምህርቱን ለሚከታተሉ ተማሪዎች፣ ለመምህራን እና ለተለያዩ የትምህርት ባለሙያዎች ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ፈተናዎች አንድ መርሃ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሰጡ በመሆናቸው ተፈታኝ ተማሪዎች ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ መዘዋወር መቻል አለመቻላቸውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያግዙ እንጂ እነዚህ ጠቀሜታዎች አሏቸው ብሎ ሙሉ በሙሉ ለመደምደም አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም ክልላዊ ፈተናዎች እነዚህን ጠቀሜታዎች መስጠት አለመስጠታቸውን ለማረጋገጥ ሰፊ ጥናትና ምርምር የሚያስፈልገው ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

#### ሀ. ለተማሪዎች

በአንድ የትምህርት ተቋም ውስጥ በሚደረግ የትምህርት ክንውን ወቅት ተዘጋጅተው የሚሰጡ የቋንቋ ፈተናዎች ተማሪዎች በቋንቋ ክሂሎች እና በእውቀት ዘርፎች ያላቸውን ችሎታ እንዲገመግሙ፣ እንዲያዳብሩና የመማር ፍላጎታቸው እንዲነሳሳ ያደርጋሉ በማለት Madson (1983) እና Davies (2001) ይገልጻሉ፡፡ እንደ እነዚህ ምሁራን ገለጻ ከሆነ የቋንቋ ፈተናዎች ለተማሪዎች በሁለት መልኩ ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ አንደኛው በክፍል ውስጥ አዎንታዊ አመለካከት እና ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ሁለተኛው ተማሪዎች የተለያዩ ፈተናዎችን በተፈተኑ ቁጥር በተደጋጋሚ ያጠናሉ፤ ይወያያሉ፡፡ ይህ በተደጋጋሚ የሚካሄድ ጥናትና ውይይት ደግሞ

ተማሪዎቹ በቋንቋው ብቁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Heaton (1990) የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ፣ ተማሪዎችን ለማበረታታት፣ በትምህርት ጊዜ ሊያጋጥማቸው የሚችሉትን ነገሮች ለመለየት፣ የተማሪዎችን ችሎታ ለመፈተሽ ያገለግላል ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተዘረዘሩት ገለጻዎች መረዳት የሚቻለው የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች ለፈተና ሲሉ ስለሚያጠኑ እና ከፈተና በኋላ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ ስለሚወያዩ የታላሚውን ቋንቋ እውቀት እንዲያሻሽሉና እንዲጠቀሙበት ስለሚያስችል ለተማሪዎች ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡

### ለ. ለመምህራን

መምህራን የተተኪሪውን ቋንቋ ትምህርት ለተማሪዎች ለማዳረስ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ የተጠቀሙትም ዘዴ ውጤታማ ሊሆንም ላይሆንም የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ውጤታማ መሆን አለመሆኑ ከሚረጋገጥባቸው መመዘኛ መንገዶች መካከል የቋንቋ ፈተና ቀዳሚውን ቦታ እንደሚይዝ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

Madson (1983) እና Hughes (1989) እንደሚገልጹት የቋንቋ ፈተና መምህራን በተለያየ መንገድ እራሳቸውን ይፈትሹበታል፡፡ ይኸውም ያስተማሩት ትምህርት በሚገባ በተማሪዎች አእምሮ ውስጥ ሰርጿል? ያቀድኩት እቅድ ከተማሪዎች ችሎታ ጋር የሚመጣጠን ነው ወይስ የማይመጣጠን ነው? ያስተማርሁበት የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማ ነው? እና ሌሎች መሰል ጥያቄዎችን በመጠየቅ ራሳቸውን እንዲመረምሩ ያስችላቸዋል ሲሉ፤ Brown (1994) ደግሞ ጥሩ የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች መምህራን ተማሪዎቹ በየትኞቹ የትምህርት ይዘቶች ላይ ለመማር እንደተቸገሩ በመገምገም በተቸገሩባቸው ይዘቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ሰጥተው ለማስተማር እንዲተጉ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ የቋንቋ ፈተና የቋንቋ መምህራን የማስተማር ስነዘዴ ተገቢነት ወይም የትምህርት አቀራረብ እና ውጤታማነት በመፈተሽ መርሃ ትምህርቱን፣ መማሪያ መጽሀፉን እና ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ታሳቢ ያደረገ የማስተማሪያ ዘዴን መርጠው

እንዲጠቀሙ ያግዛቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ዙሪያ ስላላቸው ፍላጎት እና እውቀት ሊደረግላቸው ስለሚገባ እገዛ በቂ እና ትክክለኛ የሆነ መረጃ ለማግኘት ይጠቅማቸዋል፡፡

### ሐ. ለትምህርት ባለሙያዎች

የቋንቋ ፈተና ለትምህርት ባለሙያዎች የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ፈተና ለትምህርት ባለሙያዎች መምህራን እያከናወኑት ያለውን ተግባራት በመከታተልና በመገምገም የትኞቹ ተግባራት መቀጠል፣ የትኞቹ ደግሞ መቀረፍ እንዳለባቸው የሚጠቁሙ መረጃዎችን ከፈተናው እንዲያገኙ፣ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ፣ ከእነሱ የሚጠበቀውን እገዛ እንዲያደርጉ እንዲሁም አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል (Madson 1983)፡፡ Bachman (1990)ም በበኩላቸው የቋንቋ ፈተና በአንድ መርሃ ትምህርት ውስጥ የሚደረጉ ክንውኖችን ለመገምገም እና አጠቃላይ በቋንቋ ጽንሰ ሀሳብ ላይ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መረጃ ምንጭነት ሆኖ ያገለግላል ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተናዎች ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የክሂል እና የእውቀት ዘርፎች ረገድ ያላቸውን ችሎታ ለመፈተሽ፣ የመማር ፍላጎታቸውን ለማነሳሳት፣ ለማነቃቃት እና ለማበረታታት እንዲሁም መምህራን እና የትምህርት ባለሙያዎች የተገበሯቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማነት ለመገምገም፣ ውሳኔ ለመስጠት ወይም ለማስተላለፍ እንደመነሻ ሀሳብ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

### 2.2.3 የፈተና አይነቶች

ፈተናዎች የተለያዩ አላማዎችን መሰረት በማድረግ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ የሚሰጡበትም አላማ መለያየት ለፈተና አይነቶች መለያየት ምክንያት እንደሆነ ብዙዎቹ የመስኩ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ለአብነት ያህል Harrison (1983) ፈተናን በአይነት በአይነት ለመመደብ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን አስመልክተው ሲገልጹ ፈተና የምንፈትንበትን ዋና አላማ ማወቅ የፈተናውን አይነት እንድንለይ ያስችለናል በማለት ያስረዱናል፡፡ ያለው (2009፣19)ም በበኩላቸው "የፈተናዎችን ይዘትና በተለይም አይነት የሚወስነው ዋናው ነገር ፈተናዎቹ

የተዘጋጁበት አላማ ነው።" በማለት ከHarrison (1983) ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልክ ይገልጻሉ። በዚህም ምክንያት በርካታ የመስኩ ምሁራን የፈተና አይነቶችን የተለያዩ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ በተለያየ ምድብ መድበዋቸው ይገኛሉ። ከዚህ ቀጥሎ የተወሰኑትን ለማየት ተችሏል።

Alderson et al. (1995) ፈተናዎች ከአላማቸው አኳያ የደረጃ ፈተና (Placement Test)፣ ሂደታዊ ፈተና (Progressive Test)፣ የብቃት ፈተና (Proficiency Test)፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic Test) እና የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test) በመባል በአምስት እንደሚመደቡ ሲገልጹ፤ ተስፋዬ (1981)፣ Harrison (1983) እና Huaghes (1989) ደግሞ የብቃት መለኪያ ፈተና (Proficiency Test)፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Appetitude Test)፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test) እና የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic Test) በማለት በአራት ይከፍሏቸዋል።

ከሚተገበሩበት ወቅት አኳያ ደግሞ መደበኛ ፈተና (Formal Test) እና ኢመደበኛ ፈተና (Informal Test) በመባል በሁለት ሲከፈሉ፤ መደበኛ ፈተና በውስጡ የብቃት መለኪያ (Proficiency) እና የችሎታ መለኪያ (Achievement) ፈተናዎችን ሲይዝ፤ ኢመደበኛ ፈተና ደግሞ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ (Diagnostic) እና የቅድመ ችሎታ መለኪያ (Appetitude) ፈተናዎችን ያካትታል በማለት Heaton (1990) ያስረዳሉ። Carroll (1990)ም በበኩላቸው የቅድመ ትምህርት (የብቃት መለኪያ እና ቅድመ ችሎታ መለኪያ)፣ የትምህርት ጊዜ (ጥንካሬና ድክመትን መለኪያ) እንዲሁም የድህረ ትምህርት ፈተናዎች በማለት በሶስት ይመድቧቸዋል።

ሌላው መስፈርት ከአቀራረብ አኳያ ሲሆን ፈተናዎች ከአቀራረባቸው አንጻር የምርምር ፈተና (Subjective Test) እና የምርጫ ሰጪ ፈተና (Objective Test) በመባል በሁለት ይከፈላሉ (Bachman 1990)።

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የፈተና አይነቶችን በምድብ በምድብ ለመከፋፈል ብዙዎቹ የመስኩ ምሁራን አላማን መሰረት ሲያደርጉ፤ የተወሰኑት ደግሞ የሚተገበሩበትን ጊዜ እና የሚቀርቡበት ስልት መሰረት አድርገዋል። ይሁን እንጂ የምሁራኑን አከፋፈል ስንመለከት የፈተና አይነቶችን ጠቅልሎ እና ዘርዝሮ ከማቅረብ በስተቀር መሰረታዊ የሆነ ልዩነት

አይታይባቸውም፡፡ በመሆኑም የፈተና አይነቶችን ጠቅለል ባለ ሁኔታ የብቃት መለኪያ ፈተና፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና እና የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና በመባል በአራት ይከፈላሉ ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ የቀረቡት የፈተና አይነቶች ማንኛውንም የትምህርት አይነት መሰረት ያደረጉ ሲሆን፤ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ አላማዎች ስራ ላይ ይውላሉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ክልላዊ ፈተናዎች በባህሪያቸው በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ስር የሚካተቱ በመሆናቸው ቀጥሎ በችሎታ መለኪያ ፈተና ላይ ብቻ በማተኮር ምንነቱን፣ የሚሰጥበትን ጊዜ እና የይዘት አመራረጡን ለማየት ተሞክሯል፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች አንድን የቋንቋ ትምህርት ሲማሩ ከቆዩ በኋላ የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ በአመቱ ወይም በመንፈቅ አመቱ መጨረሻ ላይ የሚሰጥ እንደሆነ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ Hughes (1989፣10) ስለችሎታ መለኪያ ፈተና ምንነት ሲገልጹ ተማሪዎች የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዷቸው ለመፈተሽ የቋንቋውን መርሃ ትምህርት አላማ መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ምሁሩ አክለውም የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተናዎች አላማ የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የትምህርት ይዘቶች መፈተሽ መሆኑ ከችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የሚለያቸው ይሁን እንጂ ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ላይ መመስረታቸው እና ተማሪዎች የተወሰኑ የትምህርት ይዘቶችን ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ የሚሰጡ መሆናቸው ሁለቱንም የሚያመሳስሏቸው ባህርያት እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡

Heaton (1990፣14)ም በበኩላቸው የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በአንድ የቋንቋ መርሃ ትምህርት ወይም መማሪያ መጻህፍ ውስጥ የተካተቱትን እና ተማሪዎች የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች ሊወክሉ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ስለሆነም ከሌሎች የፈተና አይነቶች ይልቅ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት እና የትኞቹ የትምህርት ይዘቶች መካተት እንዳለባቸው ለመወሰን ከፍተኛ ጥቃቄን የሚጠይቅ የፈተና አይነት ነው ይላሉ፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ይዘት አመራረጥ በተመለከተ Madson (1983፣32) በመርሃ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ባሉት ይዘቶች ላይ ማተኮር አለባቸው ሲሉ፤ Hughes (1989፣25)፣ Weir (1993፣5)፣ Brown (1994፣259)፣ Bachman (1990፣25) እና የመሳሰሉት ደግሞ በመርሃ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በተካተቱት አላማዎች ላይ መመስረት እንዳለባቸው ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ Harrison (1983፣137) እነዚህን ሁለት አከራካሪ ሀሳቦች ማስማማት በሚችል መልክ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ይዘት ለመምረጥ በመርሃ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱትን ይዘቶች ተገቢነት መፈተሽ እና ተማሪዎች እንዲተገብሯቸው የታቀዱትን አላማዎች መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል ይላሉ።

በአጠቃላይ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ከተወሰነ የመማር ማስተማር ሂደት በኋላ የሚሰጥ ሲሆን፤ ተማሪዎች የተማሯቸውን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ምን ያህሉን እንደተረዷቸው እና ከታሰቡት አላማዎች መካከል ምን ያህሉ ከግብ እንደደረሱ ወይም እንዳልደረሱ ለማወቅ ይረዳል። ስለሆነም ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ በመርሃ ትምህርቱም ሆነ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱትን የትምህርት ይዘቶች በአይነትም ሆነ በመጠን የሚያንጸባርቁ እና የሚወክሉ መሆን አለባቸው።

### 2.2.4 የጥሩ ፈተና መመዘኛ መስፈርቶች

የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች አላማቸውን ከግብ እንዲያደርሱ በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ይህንንም ለማድረግ የጥሩ ፈተና መመዘኛ መስፈርቶችን ማወቅና መሰረት ማድረግ ያስፈልጋል። የጥሩ ፈተና መመዘኛ መስፈርቶችን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ ምድብ ሲከፋፍሏቸው ይስተዋላሉ። ለምሳሌ ያህል Heaton (1975) እና ያለው (2009) አስተማማኝነት (Reliability) እና ተገቢነት /ትክክለኛነት/ (Validity) በማለት በሁለት ሲመድቧቸው፤ Harrison (1983) እና Brown (1994) ደግሞ አስተማማኝነት (Reliability)፣ ተገቢነት (Validity) እና ተተግባሪነት (Practicality) በመባል በሶስት ይከፈላሉ ይላሉ። ነገር ግን ይህ ጥናት በተገቢነት ላይ ብቻ የሚያተኩር በመሆኑ ቀጥሎ የተገቢነትን /የትክክለኛነትን/ ምንነት በዝርዝር ለማየት ተሞክሯል።

## ሀ. የተገቢነት ምንነት እና አይነቶች

ተገቢነት ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች መካከል አንዱ ሲሆን፤ አንድ ፈተና በጥራት ተዘጋጅቶ በመቅረብ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጥ ከሚያስችሉ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ተገቢነት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ብዙዎቹ ምሁራን ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ይገልጹታል፡፡ ለምሳሌ Harrison (1989) እና ያለው (2009) አንድ ፈተና ተገቢነት ወይም ትክክለኛነት አለው የሚባለው ለመለካት የታሰበውን ነገር በተገቢው ሁኔታ መመዘን ሲችል ስለሆነ አንድ ፈተና ለመለካት ከታሰበው አላማ ውጪ መሆን የለበትም በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ ያለው (2009፣231-232) እንደሚከተለው በምሳሌ ያስረዳሉ፡፡

> አንድ ተመራማሪ የ20 ልጆችን ቁመት በአንድ ሜትር በመለካት የቁመታቸውን ልኬት አገኘ፡፡ በማጠቃለያው ላይ "የልጆቹ አማካይ ቁመት 140 ሳ.ሜ ሲሆን ይህ የሚያመለክተው ክብደታቸው በመጠን ከፍ ያለ መሆኑን ነው፡፡" ቢል የተነሳበትን አላማ መሳት ነው፡፡ መለካት የተፈለገው ነገርና ተለክቶ የተገኘው መረጃ በሚጣጣምና በሚስማማ መልክ ሊተረጎምና ሊብራራ ይገባል፡፡ ስለቁመት መረጃ ሰብስቦ ስለክብደት መደምደሚያ ላይ መድረስ አግባብ አይደለም፡፡ በዚህ መሰረት የሚካሄድ ጥናት የሚጨምረው እውቀትም ሆነ የሚፈታው ችግር የለም፡፡

ስለዚህ ሁሉም የፈተና አዘጋጆች የሚያዘጋጁት ፈተና ተገቢነት ያለው መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ፈተና ተገቢነት ከሌለው የፈተናው ውጤት የተዛባ ስለሚሆን የታሰበውን ግብ አይመታም (Alderson et al. 1995):: በአጠቃላይ አንድ ፈተና ተገቢነት አለው የምንለው ፈተናው ለመለካት የታሰበውን የቋንቋ ትምህርት ይዘት (የቋንቋ ክሂል ወይም የእውቀት ዘርፎች) በትክክል መመዘን ሲችል ነው፡፡

የተገቢነት አይነቶች ከሚቀርቡበት አላማ እና ከሚፈለገው የመረጃ አይነት አንጻር በተለያዩ ምድቦች እንደሚከፈሉ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ ያለው (2009፣232) ተገቢነትን ትክክለኛነት የሚል ስያሜ ሰጥተው ግልብ ትክክለኛነት (Face Validity)፣ ይዘት ተኮር ትክክለኛነት (Content Validity)፣ መስፈርት ተኮር ትክክለኛነት (Criterition Validity) እና ቲዎሪ ተኮር ትክክለኛነት (Construct Validity) በማለት በአራት ሲከፋፍሏቸው፤ Bachman (1990) እና Alderson et al. (1995) ደግሞ ይዘት ተኮር ተገቢነት (Content Validity)፣ ቲዎሪ ተኮር ተገቢነት (Construct Validity) እና የመስፈርት አመልካች ተገቢነት (Criterition Reference Validity) በማለት በሶስት ይመድቧቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ Harrison (1983) ከላይ ከተዘረዘሩት የተገቢነት አይነቶች መካከል የቋንቋ መምህራን ትኩረት የሚሰጧቸው እና የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ለመገምገም የሚያገለግሉ ይዘታዊ ተገቢነት (Content Validity) እና ግልብ ተገቢነት (Face Validity) የሚሉት ናቸው በማለት ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በችሎታ መለኪያ (በማጠቃለያ) ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ላይ በመሆኑ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል፡፡

አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው ፈተናው ለታላሚው የክፍል ደረጃ ከተዘጋጀው የመርሃ ትምህርት ይዘት ጋር ግንኙነት ሲኖረው ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ፈተናው በጥያቄነት ያካተታቸው የትምህርት ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ወይም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ካላቸው ሽፋን ጋር በአይነትም ሆነ በመጠን ተመሳሳይ የሆነ ውክልና ሲኖራቸው እና በትክክል ማንጸባረቅ ሲችሉ ነው (Gronlund 1981፣ Finocchiaro and Brumfit 1983፣ Harrison 1983)፡፡ ስለዚህ አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ፈተናው በውስጡ የያዛቸው ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ ከተካተቱት ይዘቶች ጋር ትክክለኛ ወካይ መሆናቸውን መፈተሽ ነው፡፡

Hughes (1989) እና Alderson et al. (1995) ፈተናዎች መሰረት በሚያደርጓቸው መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች ወካይ ናሙናዎች ሆነው የሚቀርቡ ከሆነ የይዘት ተገቢነት አላቸው ይባላል በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ተገቢነት ያላቸው ፈተናዎች ተማሪዎች እና መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያካሂዱትን የመማር ማስተማር ተግባር በትክክል የሚያንጸባርቁ ስለሆነ ተማሪዎች የተማሯቸው ሁሉም ይዘቶች እንደተሰጣቸው የትኩረት ደረጃ በፈተናው ውስጥ ሊካተቱ ይገባል (Brown 1994)::

በአጠቃላይ የይዘት ተገቢነት ተፈታኝ ተማሪዎች አንድን የትምህርት ይዘት በተማሩት የድግግሞሽ መጠን መፈተን እንዳለባቸው እና ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ ወይም በመማሪያ መጻህፉ ውስጥ ለቀረቡት ይዘቶች ትክክለኛ ወካይ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በመሆኑም የይዘት ተገቢነት ያለው የቋንቋ ፈተና ለማዘጋጀት በመርሃ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱትን የትምህርት ይዘቶች የተሰጣቸውን ሽፋን መሰረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የአንድን ፈተና የይዘት ተገቢነት ለመፈተሽ ደግሞ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም እንደሚገባ Alderson et al. (1995) እና Weir (2005) ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህም ስልቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱትን ጥያቄዎች ይዘት በመርሃ ትምህርቱ ወይም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች ጋር ማነጻጸር (Alderson et al. 1995፣193)፡፡
- በፈተናው ውስጥ መካተት የሚገባቸው ሁሉም የትምህርት ይዘቶች እንደተካተቱ እና ተገቢ የሆነ ሽፋን ወይም ውክልና እንዳገኙ መመርመር (Weir 2005፣25)፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት ለመፈተሽ ከላይ የቀረቡትን የመፈተሻ ስልቶች መሰረት አድርጓል፡፡

### 2.2.5 የቋንቋ ትምህርት እና የቋንቋ ፈተና ተዛምዶ

የቋንቋ ትምህርት እና የቋንቋ ፈተና የማይነጣጠሉ የአንድ ቋንቋ የመማር ማስተማር ተግባራት ናቸው፡፡ በመሆኑም በሁለቱ መካከል ጥብቅ የሆነ ቁርኝነት ወይም ትስስር ሊኖር እንደሚገባ በተለያዩ ምሁራን ዘንድ ይታመናል፡፡

Baker (1989) ፈተና በቋንቋ ትምህርት ሂደት  ውስጥ አይቀሬ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ አካላት በመማር ማስተማሩ ዙሪያ የሚያስፈልጉ መረጃን ለማግኘትና የሚከናወኑ ስራዎችን ለማረጋገጥ እንዲሁም ለመገምገም መሰረቱ ፈተናዎች ስለሆኑ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ Harrison (1983) በበኩላቸው ትምህርት ካለ ፈተና አለ፤ ትምህርት ደግሞ ትርጉም የሚኖረው ፈተና ሲኖር በመሆኑ የቋንቋን ትምህርትና የቋንቋን ፈተና ከአንድ የመማር ማስተማር ተግባር ለየብቻ ነጣጥሎ ማየት አይቻልም በማለት ያስረዳሉ፡፡

Brown (1994) ደግሞ የቋንቋ ፈተና የቋንቋ መርሃ ትምህርት ቀጣይነት እንዲኖረውና ከጊዜ ወደጊዜ እንዲሻሻል ወይም እንዲዳብር የሚያደርግ በመሆኑ የማስተማሩን ስራ መደበኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት አንድ መርሃ የትምህርት የተሳካ ሆኖ የተፈለገው አላማ ግብ እንዲመታ ለማድረግ ፈተና ከፍተኛ ድርሻ ስለለው ነው ይላሉ፡፡ ይህ

ሀሳብ ደግሞ የአንድን መርሃ ትምህርት አላማ ለመሳካት ፈተና እንደሚያስፈልግ እና ፈተና ከሌለ ትምህርት ቀጣይነት ሊኖረው እንደማይችል የሚያመለክት ነው፡፡

Heaton (1975) የፈተናን እና የትምህርትን ግንኙነት ሲገልጹ ፈተና የመማር ማስተማሩን ስራ የሚያጎለብት ሲሆን፤ የመማር ማስተማሩ ተግባር ደግሞ የአንድን ፈተና ውጤታማነት እንደሚያረጋግጥ ይገልጻሉ፡፡ ይህም ፈተና እና የመማር ማስተማሩ ተግባር እርስ በርስ ተደጋጋፊ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ለቋንቋ ትምህርት ፈተና ምንጩ ወይም መሰረቱ በክፍል ውስጥ የሚከናወነው ትምህርት እንደሆነ ሁሉ ፈተና ደግሞ ለመማር ማስተማሩ ሂደት መሻሻል እንደግብአት ስለሚያገለግል ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች በቅድመ መማር፣ በመማር ሂደት እና በድህረ መማር ጊዜ የሚሰጡ ቢሆንም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መሰረት በማድረግ የሚሰጡ ፈተናዎች ግን በመማር ሂደት እና በድህረ መማር ጊዜ የሚሰጡ ናቸው (Harrison 1983፣ Hughes 1989፣ Alderson et al. 1995፣ Brown 1996)፡፡ በመሆኑም ይህ አይነቱ ፈተና ተማሪዎች ከተማሩት የትምህርት ይዘት ጋር ያለው ዝምድና የጠበቀ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንን አስመልክተው ተስፋዬ (1981) ፈተና ተማሪዎች የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች ማወቅ አለማወቃቸውን መለያ ስለሆነ መፈተን ያለባቸውም የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች ብቻ ሊሆን ይገባል በማለት ይገልጻሉ፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት በደቡብ ብሄር ብሀረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በቀረቡት የትምህርት ይዘቶች አማካኝነት ተማሪዎች ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ መዘዋወር የሚያስችል እውቀት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን ለመለካት ወይም ለመመዘን እንዲሁም ውሳኔ ለማስተላለፍ ታስበው የሚሰጡ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የቋንቋ ትምህርት እና የቋንቋ ፈተና የጠበቀ ዝምድና ያላቸው፣ እርስ በርስ የሚደጋገፉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ፈተናዎች መሰረት ካደረጓቸው የመርሃ ትምህርት እና የመማሪያ መጻህፍት ይዘቶች ጋር ጥብቅ የሆነ ትስስር ሊኖራቸው እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡

Hughes (1989) እንደሚገልጹት የቋንቋ ፈተና ይዘቶች በተለይም የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መሰረት ከሚያደርጉት መርሃ ትምህርት እና መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተውጣጡ መሆን አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ለተማሪዎች የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ምንጮቻቸው ለደረጃው የተዘጋጁት መርሃ ትምህርት ወይም መማሪያ መጽሀፍ እንደመሆናቸው መጠን ፈተናዎቹም መርሃ ትምህርቱንና መማሪያ መጽሀፉን መሰረት ሊያደርጉ ግድ ይላል፡፡

ከመርሃ ትምህርቱ ወይም ከመማሪያ መጽሀፉ ጋር የይዘት ዝምድና ያላቸውን የፈተና ጥያቄዎች ለማዘጋጀት የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Tabel of Specification) መጠቀም ይገባል፡፡ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ የትምህርት ይዘቶችን እና ዝርዝር አላማዎችን የያዘ ባለሁለት ረድፍ ቻርት ሆኖ ለመፈተን የተፈለገውን የትምህርት ይዘት እና ወካይ ጥያቄዎችን የያዘ ነው (Gronlund 1981፣ ዳንኤል 2006)፡፡

Alderson et al. (1995)ም በበኩላቸው የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ ከቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መካከል የትኞቹን የቋንቋ ይዘቶች ለመፈተን እንደተፈለገ እና ከእያንዳንዱ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ምን ያህል ጥያቄዎች መካተት እንደቻሉ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፈተና ውስጥ መካተት ያለባቸው ይዘቶች ሳይካተቱ እንዳይቀሩ፤ ጠቃሚና ትኩረት በተሰጣቸው የትምህርት ይዘቶች ላይ እንዲተኮር እንዲሁም አላስፈላጊ ድግግሞሽ እንዳይኖር ለማድረግ ያገለግላል በማለት ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ በመርሃ ትምህርቱ የተነደፉትን የትምህርት አላማዎች እና ተማሪዎች የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች መሰረት ያደረጉ የፈተና ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት፣ ፈተናው በትኞቹ የትምህርት ይዘቶች ላይ እንደሚያተኩር ለመጠቆም ይረዳል፡፡

### 2.2.6 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች

ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ስርኣት የሚያሳይ ሳይንስ ሲሆን በውስጡ የተለያዩ ዝርዝር ይዘቶችን ያቀፈ ነው፡፡ ይህን አስመልክተው Bachman (1990) በቋንቋ ፈተና ተማሪዎች በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች እንዲሁም በሰዋስው እና በስነጽሁፍ የእውቀት

ዘርፎች ያላቸው ችሎታ ይመዘናል፡፡ ከቋንቋ ችሎታዎች (ብቃቶች) መካከል አንዱ የሆነው የሰዋስው ችሎታም የስነድምጽ፣ የስነምእላድ፣ የአረፍተ ነገር ስርአት እና የስነፍቺ ችሎታዎችን እንደሚያካትት ይገልጻሉ፡፡

Purpura (2004) ደግሞ የሰዋስው እውቀት ሰዋስዋዊ ቅርጽ እና ሰዋስዋዊ ፍቺ የሚሉትን ሁለት ክፍሎች የያዘ ነው፡፡ ሰዋስዋዊ ቅርጽ የስነድምጽ፣ የምእላዶች እና የቃላት መዋቅራዊ ቅርጾች ስብስብ ሲሆን፤ ሰዋስዋዊ ፍቺ ደግሞ በቃላት፣ በሀረጋት እና በአረፍተ ነገሮች ደረጃ ያሉ ውህድ አሃዶችን ፍቺ የሚመለከት እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

ሰዋስው የቋንቋ ስርአትን የሚያመለክት በመሆኑ የሰዋስው ትምህርት ዋና አላማም የአንድን ቋንቋ ስርአት ከድምጽ አስካክ አንስቶ እስከ ሀረግ አመሰራረት ድረስ ያለውን መዋቅር ማሳየትና ማሳወቅ ነው (ባየ 1987፣8-9)፡፡ ጌታሁን (2011፣xi)ም በበኩላቸው ስለሰዋስው ፍቺ እና በውስጡ ስለሚይዛቸው ዘርፎች የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ሰዋስው ከቋንቋ ጥናቶች ውስጥ ስርአትን የሚመለከተው ክፍል ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል፡፡ አንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ `እውቀት` የሚጠቁመውና በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለው ችሎታ ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳባዊ እይታ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሊያውቅና ሊጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስው አእምሯዊ እሳቤ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለቋንቋ ስርኣትና መዋቅር የሚያደርጉትን ከስነድምጽ እስከ ስነሀረግ ያለውን ገለጻ የሚጠቁመው ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት የመስኩ ምሁራን ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው ሰዋስው ሰፊ ጽንሰ ሃሳብን የያዘ እና በአንድ ቋንቋ ውስጥ ካለ ቅንጣት አሃድ ጀምሮ እስከ ትልቁ አሃድ ድረስ ያሉትን መዋቅሮች (የስነድምጽን፣ የስነምእላድን፣ የስነአገባብን እና የስነፍቺን) የአጠቃቀም ስርኣት አስመልክቶ ትክክለኛና ሳይንሳዊ ተቀባይነት ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም የሚተነትን መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስነድምጽ፣ ስነምእላድ፣ ስነአገባብ እና ስነፍቺ የሚሉ አራት ዘርፎች ያሉት እና እነዚህም አራት ዘርፎች በውስጣቸው የተለያዩ ንኡሳን ይዘቶችን ያቀፉ መሆናቸውን ለመረዳት አያዳግትም፡፡

በዚህ መሰረት የዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እንዲሁም በክልላዊ ፈተናዎቹ ውስጥ

የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች በመለየት በአራቱ አበይት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመከፋፈል ተፈትሸዋል፡፡

### 2.2.7 የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች አቀራረብ መርህ

በአንድ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ የጥያቄ ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ወካይ ስለሆኑ ብቻ ጥሩ ፈተና ለማዘጋጀት ተችሏል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎች የግል ባህሪ፣ እድሜ፣ ጾታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ወዘተ. በጥያቄ አቀራረብ ስልት ላይ ተጽእኖ ስለሚያሳድሩ እነዚህን ነገሮች መሰረት በማድረግ የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለመፈተን የተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በዋናነት የሚታወቁት የጥያቄ አቀራረብ ስልቶች ድርሰታዊ እና ምርጫ ሰጪ ሲሆኑ የሰዋስው ጥያቄዎችን ለመፈተን ግን አብዛኛውን ጊዜ ምርጫ ሰጪ የአቀራረብ ስልትን እንደምንጠቀም Heaton (1975) ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት በምርጫ መልክ በሚቀርቡ የፈተና ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ቀጥሎ የምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልትን ምንነት ብቻ ለማየት ተሞክሯል፡፡

በምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልት የሚቀርቡ ጥያቄዎች መሪ ጥያቄውን መሰረት በማድረግ ለጥያቄው መልስ የሚሆነው አማራጭ እና ሌሎች አሳሳች አማራጮች ተዋቅረው የሚቀርቡበት የአቀራረብ ስልት ነው፡፡ ይህን አስመልክተው Heaton (1975) እና Weir (2005) የምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልት በአንድ መሪ ጥያቄ እና ለጥያቄው መልስ ይሆናሉ ተብለው በሚቀርቡ አራት ወይም አምስት አማራጮች ተዋቅሮ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ የሚመለስበት ስልት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

የምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልት ብዙ ጥያቄዎችን አካቶ ከመያዙ ባሻገር በአንድ ጊዜ የተለያዩ ይዘቶችን ለመመዘን ስለሚረዳ ጠቀሜታው የጎላ ነው (Kopriva 2008)፡፡ Fulcher and Davidson (2007)ም በበኩላቸው የምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልት ለአስተራረም አመቺ በመሆኑ በማሽን ለማረም አያዳግትም፡፡ ስለሆነም ተፈታኞችን ያለ አድሎ ለመመዘን ይረዳል በማለት ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው በምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልት የሚቀርቡ ጥያቄዎች አንድን መሪ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ከተሰጡ አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን አማራጭ ለመምረጥ በሚያስችል መልክ የሚቀርቡ መሆናቸውን ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች አቀራረብ ስልት ወይም መርህ ሲባል የፈተና አዘጋጆች አንድን ጥያቄ በምርጫ መልክ ሲያዘጋጁ ምን ምን ነጥቦችን መሰረት ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ይህን አስመልክተው የተለያዩ የመስኩ ምሁራን የተለያዩ መርሆች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ Brown (1996፣48) የፈተና ጥያቄዎችን በምርጫ ሰጪ የአቀራረብ ስልት ለማቅረብ ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ መርሆች ውስጥ የሚከተሉትን ይጠቅሳሉ፡፡

- በአንድ መሪ ጥያቄ ውስጥ ከቀረቡት አራት ወይም አምስት አማራጮች መካከል አሳሳች (Distracters) ሆነው የገቡት አማራጮች ዋናውን መልስ የማሳሳት አቅም ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡
- ፍጹማዊ የሆኑ ቃላትን ማለትም እንደዘወትር፣ ፈጽሞ፣ አብዛኞቹ፣ ብቻ፣ የመሳሰሉ ቃላትን አለመጠቀም፡፡
- የመሪው ጥያቄ ማእከላዊ ሀሳብ ግልጽ በሆነ መልኩ መቅረብ አለበት፡፡
- በመሪው ጥያቄ ላይ የሚቀርበው ሀሳብ ነጠላ የሆነና ወደ መልስ የሚያመራ አላስፈላጊ የሆነ ጠቋሚ ሀሳብን ያልያዘ መሆን አለበት፡፡
- አማራጮች ተመሳሳይ ይዘት፣ ቅርጽ እና አወቃቀር ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- አላስፈላጊ የሆነ ድግግሞሽ መወገድ አለበት፡፡
- የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች መቅረብ የለባቸውም፡፡
- ሁሉም መልስ ናቸው፣ መልስ አልተሰጠም፣ ሀ እና ለ መልስ ናቸው፣ ወዘተ. የሚሉ አማራጮች እንዳይኖሩ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡
- ጥያቄዎቹ ቀድሞ ወይም ቀጥሎ ከመጣ ወይም ከሚመጣ ጥያቄ ጋር ተያያዥ መሆን የለባቸውም፡፡
- እያንዳንዱ የፈተና ጥያቄ አንድ መልስ ብቻ ሊኖረው ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ የተለያዩ ቀደምት ጥናቶች ውጤት እንደሚያመለክቱት የተለያዩ የፈተና አዘጋጆች የፈተና አቀራረብ መርሆችን ባለማወቅም ይሁን በቸልተኝነት ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ከላይ የተጠቀሱትን መርሆች ያሟሉ ፈተናዎችን ሲያዘጋጁ አይስተዋሉም፡፡ ይህ ደግሞ የፈተናዎቹን ሳቢነት፣ ግልጽነት እና ተገቢነት በመቀነስ የታሰበው አላማ ከግብ እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ይህንን ችግር ለመቆጣጠር ማንኛውም በምርጫ መልክ የሚዘጋጅ ፈተና ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎች መሰል መርሆችን መሰረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

እንደ Heaton (1975) እና Brown (1996) ገለጻ በምርጫ ሰጪ አቀራረብ ስልት የሚቀርቡ የፈተና ጥያቄዎች መሪ ጥያቄ፣ ትክክለኛ መልስ እና አሳሳች አማራጮች የሚባሉ ሶስት ክፍሎች አሏቸው፡፡ መሪው ጥያቄዎች በተሟላ ሀሳብ፣ ባልተሟላ ሀሳብ እና በጥያቄ መልክ የሚቀርቡ ሲሆን፤ ሊጠየቅ የተፈለገውን ተግባር በግልጽ የሚያቀርቡ እና አላስፈላጊ የሆነ ጥቆማ የማይሰጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሌላኛው ክፍል ትክክለኛው መልስ ሲሆን ከአሳሳች አማራጮቹ ጋር እኩል የሆነ ርዝማኔ ያለው፣ አሻሚ ያልሆነ እና ለመሪው ጥያቄ ከሌሎች አማራጮች በበለጠ ሁኔታ መልስ ሊሆን በሚችል ሁኔታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ አሳሳች አማራጮች ደግሞ ሳቢ፣ ትክክለኛውን መልስ የመምሰል እና ከትክክለኛው መልስ ለመለየት የሚያዳግቱ ሆነው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህም ጥናት እነዚህን መርሆች መሰረት በማድረግ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተዘጋጁ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ሞክሯል፡፡

## 2.3 የሀገር ውስጥ የቀደሙ ጥናቶች ዳሰሳ

የዚህ ጥናት አድራጊ ለጥናት ከመረጠው ርእሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች ለመዳሰስ ሞክሯል፡፡ በዳሰሳውም በአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ዙሪያ የተሰሩ የተለያዩ ጥናቶች እንዳሉ ተመልክቷል፡፡ ለአብነት ያህል አበበች (2004) “ከ1998 እስከ 2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው በቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ”፣ መሰረት (2005) “በትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው ከ1999 እስከ 2004 ዓ.ም

በተሰጡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ"፣ ሙሉጸሀይ (2005) "ከ2000 ዓ.ም እስከ 2004 ዓ.ም በ8ኛ ክፍል ሞዴል ፈተና እና ክልላዊ ፈተና ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ያለውን የይዘት አቀራረብ ዝምድና ፍተሻ"፣ የትምወርቅ (2007) "ከ2004 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ተዘጋጅተው የቀረቡትን የ8ኛ ክፍል ሞዴልና ክልላዊ ፈተናዎች የይዘት ተዛምዶና ተገቢነት ፍተሻ" እና ኤልሳቤጥ (2009) "በአፋር ክልል ከ2004 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ለ8ኛ ክፍል የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ከሞዴል ፈተናዎች ጋር ያላቸውን የይዘት አቀራረብ ልዩነት በንጽጽር" በሚሉ ርእሶች ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡

ከእነዚህም ጥናቶች መካከል የሙሉጸሀይ (2005)፣ የኤልሳቤጥ (2005) እና የየትምወርቅ (2007) ጥናቶች ለ8ኛ ክፍል በተሰጡት የክልላዊ እና የሞዴል ፈተናዎችን የይዘት ዝምድና መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የሙሉጸሀይ ጥናት በሞዴል እና በክልላዊ ፈተናዎች ላይ መሰረት ያደረገ ቢሆንም በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ዝምድና መገምገም ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ የአበበች (2004) እና የመሰረት (2005) ጥናቶች ደግሞ በክልላዊ ፈተናዎቹ ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነትና አቀራረብ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር የቀረበ ዝምድና አላቸው፡፡

ስለሆነም አበበች (2004) "ከ1998 እስከ 2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ አማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ በተጠቀሰው ክልልና አመተ ምህረት በቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎችን አቀራረብ መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ለጥናቱ በናሙናነት የተወሰዱ 154 የሰዋስው ጥያቄዎች በሙሉ መርሃ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ እና ከተወሰኑ ጥያቄዎች በስተቀር አብዛኞቹ የፈተና አቀራረብ መርሆችን ተከትለው እንደቀረቡ ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተወሰኑ የትምህርት ይዘቶች በፈተናዎቹ ውስጥ ውክልና እንዳላገኙ እና የተካተቱትም ይዘቶች ቢሆኑ በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ውስጥ በተሰጣቸው የትኩረት ደረጃ መሰረት እንዳልቀረቡ በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ አስፍረዋል፡፡

የመሰረት (2005) ጥናት ደግሞ “በትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው ከ1999 እስከ 2004 ዓ.ም በተሰጡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ” በሚል ርእስ የቀረበ ሲሆን፤ አጥኚዋ ተተኳሪ በሆኑት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች 225 መሆናቸውን ገልጸው ከእነዚህ ጥያቄዎች መካከል የተወሰኑት የይዘት ተገቢነት ያላቸው ቢሆንም አብዛኞዎቹ የሰዋስው ጥያቄዎች ግን የይዘት ተገቢነት የሌላቸው እና የአቀራረብ ችግር ያለባቸው እንደሆኑ በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

ምንም እንኳን የአበበች (2004) እና የመሰረት (2005) ጥናቶች በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ላይ በማተኮራቸው ምክንያት ከዚህ ጥናት ጋር የቀረበ ዝምድና አላቸው ቢባልም ይህ ጥናት ተተኳሪ ያደረጋቸው ክልላዊ ፈተናዎች፣ መማሪያ መጻህፍት፣ ፈተናዎቹ ከተዘጋጁበት ክልልና አመተ ምህረት አንጻር ሲታይ ከሌሎቹ ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል፡፡

# ምእራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ቅይጥ የምርምር ዘዴ ወይም አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች ተመራጭ ሆነዋል፡፡ ዘዴዎቹም ተመራጭ የሆኑበት ምክንያት ያለው (2009፣17-18) እንደሚገልጹት መጠናዊ የምርምር ዘዴ መረጃዎች በመጠን ወይም በቁጥር የሚገለጹበት እና በስታቲስቲካዊ ዘዴ የሚተነተኑበት ሲሆን፤ አይነታዊ የምርምር ዘዴ ደግሞ መረጃዎች በትረካ ወይም በገለጻ መንገድ ተተንትነው የሚቀርቡበት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ዙሪያ የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥር እና በትረካ ወይም በገለጻ መንገድ ተተንትነው ስለሚቀርቡ ሁለቱን ዘዴዎች አጣምሮ መጠቀሙ አመች ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

## 3.2 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት ፈትሿል፡፡ ጥናቱ ይህንን ተግባር ለማከናወን የተጠቀማቸው የመረጃ ምንጮች በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. የቀረቡት የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናዎች፣ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጽሀፍት እንዲሁም የክልሉ ትምህርት ቢሮ የስርአተ ትምህርትና የፈተናዎች ዝግጅት ክፍል ሃላፊ ናቸው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ለ8ኛ ክፍል በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት ለመፈተሽ የጥናቱ ናሙናዎች በሚከተሉት ዘዴዎች ተመርጠዋል፡፡

### 3.3.1 የፈተናዎች ናሙና አመራረጥ

የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናን እያዘጋጀ መስጠት ከጀመረ ከአስር አመታት በላይ እንደሆነው ከክልሉ ትምህርት ቢሮ የስርአተ ትምህርትና የፈተናዎች ዝግጅት ክፍል ሃላፊ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በምእራፍ አንድ በንኡስ ርእስ 1.5 ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የቀደሙት መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት በ2007 ዓ.ም. በአዲስ መልክ ተሻሽለው ከ2010 ዓ.ም. ጀምረው ስራ ላይ በመዋላቸው እና ክልላዊ ፈተናዎቹም አዲሶቹን የማስተማሪያ መሳሪያዎች መሰረት አድርገው የተዘጋጁ በመሆናቸው ምክንያት በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. ተዘጋጅተው በቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ እንዲመረጡ ሆነዋል፡፡

### 3.3.2 የክልልና የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በሀገራችን ከሚገኙ ዘጠኝ ክልሎች ውስጥ ይህ ጥናት ከጊዜ እና ከጉልበት ውስንነት አንጻር በአንድ ክልል ላይ ብቻ ተወስኖ በ8ኛ ክፍል ላይ አተኩሯል፡፡ ተተኳሪው ክልልም ሆነ የክፍል ደረጃ በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሊመረጡ ችለዋል፡፡ ምክንያቱም አመቺ ናሙና አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ በሚፈልገውና በሚመቸው ርእሰ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ የሚመርጥበት የአመራረጥ ዘዴ በመሆኑ ነው (ያለው 2009፣135)፡፡

አጥኚው ተተኳሪውን ክልል የመረጠበት ምክንያት የቀደምት ጥናቶችን ዳሰሳ ባደረገበት ወቅት በተለያዩ ክልሎች በተለያዩ ጊዜያት በተሰጡ ክልላዊ ፈተናዎች ላይ የተሰሩ ጥናቶች እንዳሉ

ለማስተዋል ቢችልም በተተኳሪው ክልል በተሰጡ ክልላዊ ፈተናዎች ላይ ግን ምንም አይነት የተካሄደ ጥናት ባለማግኘቱ ነው፡፡ የክፍል ደረጃውን የመረጠበት ምክንያት ደግሞ በተተኳሪው ክልል በክልል ደረጃ የሚዘጋጁ ፈተናዎች የሚሰጡት ለ8ኛ ክፍል ብቻ በመሆኑ ነው፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.4.1 የሰነድ ፍተሻ

የሰነድ ፍተሻ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ምክንያቱም እንደነ Best and Khan (2002) እና Dornyei (2007) ገለጻ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚተነተኑት በቃላት ሲሆን፤ ለዚህ ደግሞ የገላጭ አትንተና ዘዴ ተመራጭ ነው ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ሰነዶችን (በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው የቀረቡትን የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች፣ ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁትን የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት) በመረጃ ምንጭነት በመጠቀም መረጃዎችን ስለሰበሰበ እና የተሰበሰቡ መረጃዎችም በትረካዊ ወይም በገለጻዊ መንገድ ተብራሩ በመሆናቸው የገላጭ አቀራረብ ስልትን ተጠቅሟል፡፡

የሁለቱ ክፍሎች መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት በሰነድ ፍተሻው የተካተቱበት ምክንያት ክልላዊ ፈተናዎቹ እነሱን መሰረት በማድረግ እንደሚዘጋጁ የክልሉ የስርአተ ትምህርትና የፈተናዎች ዝግጅት ክፍል ሃላፊ በሰጡት መረጃ በመረጋገጡ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ በተተኳሪ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች የአቀራረብ ሁኔታ እና ከመርሃ ትምህርቶቹ እንዲሁም ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ያላቸው የይዘት ተገቢነት ምን እንደሚመስል ፈትሿል፡፡

### 3.4.2 ቃለ መጠይቅ

እንደ ያለው (2009፣183) ገለጻ ቃለ መጠይቅ በአብዛኛው ውስን ለሆኑ ተጠያቂዎች ሊቀርብ የሚችልና ጥናት የሚካሄድበትን ርእሰ ጉዳይ አስመልክቶ ጥልቅ እና የተብራራ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። በዚህ ጥናትም ለጥናቱ አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ለስርአተ ትምህርትና ለፈተናዎች ዝግጅት ክፍል ሃላፊ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። የቃለ መጠይቁም አላማ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና በክልል ደረጃ መዘጋጀትና መሰጠት የጀመረው መቼ እንደሆነ፣ ክልላዊ ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ የትኞቹን የትምህርት መሳሪያዎች እና የክፍል ደረጃዎች መሰረት እንደሚያደርጉ እንዲሁም አሁን በስራ ላይ ያሉት የማስተማሪያ መሳሪያዎች መቼ ስራ ላይ እንደዋሉ ለመረዳት ነው። እነዚህንም መረጃዎች ለማግኘት እንደመነሻ የሚያገለግሉ ሰባት (7) ጥያቄዎች በአጥኚው ተዘጋጅተው ቀርበዋል።

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በአይነታዊ እና በመጠናዊ ዘዴዎች ተተንትነዋል። የትንተናው ሂደትም በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን እንደአስፈላጊነታቸው ጥቅም ላይ በማዋል በመጀመሪያ በተተኳሪ መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተመሳሳይ በመሆናቸው በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን እና በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት በቁጥርና በመቶኛ በማስላት በተናጠል የመተንተን ስራ ተሰርቷል።

በመቀጠል ያለው (2009) በተለያዩ ተለዋዋጮች መካከል ያለውን ዝምድና ለማወቅየሚያስችሉ የተለያዩ የተዛምዶ መጠን መለኪያዎች እንዳሉ በመግለጽ የተዛምዶ መለኪያ በሁለት ተለዋዋጮች መካከል ያለውን ዝምድና ወይም ግንኙነት መጠን እና አቅጣጫ ለመወሰን የሚረዳ መሆኑን ያስረዳሉ። በዚህ መሰረት በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና በፈተናዎቹ ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ያለውን የይዘት ዝምድና ለማወቅ ከተዛምዶ መጠን መለኪያዎች መካከል አንዱ በሆነው የፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመርን በመጠቀም

ዝምድናቸው ተሰልቶ በቁጥር እና በመቶኛ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ የፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመርም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

$$rxy= \frac{N\sum XY-\sum X\sum Y}{\sqrt{(N\sum X^{2}-(\sum X)^{2})(N\sum Y^{2}-(NY)^{2})}}$$

rxy= በX እና በY መካከል ያለው የተዛምዶ መጠን

N= በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ተጠኝዎች ብዛት

$\sum X^{2}$ = እያንዳንዱ ተጠኚ በX ተለዋዋጭ ላይ ያገኘው ውጤት ካሬ እየተደረገ በሙሉ ተደምሮ የሚገኝ ውጤት

$\sum Y^{2}$ = እያንዳንዱ ተጠኚ በY ተለዋዋጭ ላይ ያገኘው ውጤት ካሬ እየተደረገ በሙሉ ተደምሮ የሚገኝ ውጤት

$\sum X$ = ሁሉም ተጠኝዎች በX ተለዋዋጭ ላይ ያገኙት ውጤት አጠቃላይ ድምር

$\sum Y$ = ሁሉም ተጠኝዎች በY ተለዋዋጭ ላይ ያገኙት ውጤት አጠቃላይ ድምር

$(\sum X)^{2}$ = ሁሉም ተጠኝዎች በX ተለዋዋጭ ላይ ያገኙት ውጤት አጠቃላይ ድምር ካሬ በማድረግ የሚገኝ ውጤት

$(\sum Y)^{2}$ = ሁሉም ተጠኝዎች በY ተለዋዋጭ ላይ ያገኙት ውጤት አጠቃላይ ድምር ካሬ በማድረግ የሚገኝ ውጤት

$\sum XY$ = የእያንዳንዱ ተጠኚ በሁለቱ ተለዋዋጮች ላይ ያገኛቸው ውጤቶች እየተባዙ የተገኘው ውጤት በሙሉ ተደምሮ የሚገኝ ውጤት

0.00 — 0.19= ዝምድና የለሽ ወይም በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ

0.20 — 0.39= ዝቅተኛ ተዛምዶ

0.40 — 0.59= መካከለኛ ተዛምዶ

0.60 — 0.79= ከፍተኛ ተዛምዶ

0.80 — 1.00= በጣም ከፍተኛ (ጠንካራ) ተዛምዶ እንደሆነ ያሳያል፡፡

(ምንጭ፡- ያለው 2009)

በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ስሌት የሚገኝ የተዛምዶ መጠን ከ+1 እስከ -1 የተወሰነ ሲሆን፤ የተዛምዶ መጠኑ ከ0 ወደ+1 እየቀረበ ከመጣ የተዛምዶ መጠኑ ጠንካራ፣ አቅጣጫውም አዎንታዊ እንደሆነ የሚያሳይ ሲሆን፤ በአንጻሩ የተዛምዶ መጠኑ ከ0 ወደ-1 እየቀረበ ከሄደ የተዛምዶ መጠኑ ጠንካራ፣ አቅጣጫው ደግሞ አሉታዊ ይሆናል (ያለው 2009፣340)፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት መማሪያ መጻህፍት እና የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ዝምድና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም የተተኳሪ ጥያቄዎች አቀራረብ ከምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች አቀራረብ መርህ አንጻር ምን እንደሚመስል በቁጥርና በመቶኛ በማስፈር በገለጻ መልክ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

# ምእራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በምእራፍ አንድ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በተሰጡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡

በዚህ ምእራፍ ደግሞ የተተኳሪውን ጥናት አላማ ከግብ ለማድረስ በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበውበታል፡፡ በምእራፍ ሶስት ላይ እንደተገለጸው ይህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ከተገለገለባቸው ሰነዶች መካከል በተተኳሪው ክልል የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጽሀፍት ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጂ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በተተኳሪ መርሃ ትምህርቶቹ እና መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተመሳሳይ መሆናቸው ስለተረጋገጠ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት ለመፈተሽ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ የተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ አጭር ቅኝት፣ በተተኳሪ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ያላቸው የይዘት ዝምድና እና አቀራረብ ምን እንደሚመስል በቅደም ተከተላቸው መሰረት ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ አጭር ቅኝት

በመማሪያ መጻህፍቱ ሁለተኛ ሽፋን ላይ እንደተገለጸው በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በ2007 ዓ.ም. በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ ለክልሉ በሚስማማ አውድ መሰረት ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ መጻህፍቱ በ2007 ዓ.ም. ይዘጋጁ እንጂ ስራ ላይ የዋሉት በ2010 ዓ.ም. እንደሆነ ከክልሉ ትምህርት ቢሮ የስርአተ

ትምህርትና የፈተናዎች ዝግጅት ክፍል ሃላፊ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል። መማሪያ መጻህፍቱ በመግቢያቸው ላይ የስርአተ ትምህርቱ መሰረታዊ መርሆች፣ ከትምህርት ቤት ውጪ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ጋር ሊኖሯቸው የሚገባቸውን ትምህርታዊ ተግባራት እና በውስጣቸው የሚገኙትን ይዘቶች አደረጃጀት ያስተዋውቃሉ።

የመማሪያ መጻህፍቱን ዋና የትምህርት ክፍል አቀራረብ ስናይ ደግሞ ሁለቱም መጻህፍት እያንዳንዳቸው እኩል አስር ምእራፎች አሏቸው። እያንዳንዱ ምእራፍ ሶስት ምንባቦችን የያዘ ሲሆን፤ በአጠቃላይ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሰላሳ ምንባቦች ተካተው ይገኛሉ። ምእራፎቹ በሶስት ሳምንታት እና በዘጠኝ ቀናት የተከፋፈሉ ሲሆን፣ ሳምንቶቹ ደግሞ በሶስት ቀናት ተከፋፍለዋል። በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረበውም አጠቃላይ የአመቱ ትምህርት በሰላሳ ሳምንታት ተከፋፍሎ ቀርቧዋል።

መጻህፍቱ በውስጣቸው ስምንት ዋና ዋና የትምህርት ይዘቶችን አካተው የያዙ ሲሆን፤ ይዘቶቹም የቃላት ጥናት፣ አንብቦ መረዳት፣ ቃላት፣ ማዳመጥ፣ መናገር፣ አቀላጥፎ ማንበብ፣ መጻፍ እና ሰዋስው የሚሉት ናቸው። የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በእያንዳንዱ ምእራፍ ሶስት ጊዜ የቀረቡ ሲሆን፤ በአጠቃላይ በአስሩ ምእራፎች ውስጥ ደግሞ ሰላሳ ጊዜ ቀርበዋል። ከዚህም በተጨማሪ መጻህፍቱ በመጨረሻ ገጻቸው ላይ የቃላትን ፍቺ የሚያሳይ ሙዳየ ቃላትን እና ዋቢዎችን አካተዋል።

ይሁን እንጂ የሁለቱ መማሪያ መጻህፍት ገጽ እና በውስጣቸው የያዟቸው የትምህርት ተግባራት ብዛት የተለያዩ ናቸው። በመሆኑም የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ 237 ገጾች ያሉት ሲሆን፤ በውስጡ 361 አጠቃላይ የትምህርት ተግባራትን (ጥያቄዎችን) አካቷል። ከእነዚህም ተግባራት ውስጥ 32ቱ የሰዋስው ትምህርትን መሰረት ያደረጉ ናቸው። የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ደግሞ 255 ገጾች ያሉት ሲሆን፤ በውስጡ 419 የትምህርት ተግባራትን (ጥያቄዎችን) ያካተተ ሲሆን፤ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ 54ቱ የሰዋስው ትምህርትን መሰረት ያደረጉ እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል።

ከላይ የቀረበው ማብራሪያ የተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱን አጠቃላይ መረጃ የሚጠቁም ሲሆን፤ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና ክልላዊ

ፈተናዎቹ ውስጥ ያላቸውን የድግግሞሽ መጠን እናያለን፡፡ የሰዋስው የትምህርት ይዘቶች ስነድምጽ፣ ስነምእላድ፣ ስነአገባብ እና ስነፍቺ በመባል እንደሚከፈሉ በምእራፍ ሁለት ለማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና ክልላዊ ፈተናዎቹ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስነድምጽ፣ ስነምእላድ፣ ስነአገባብ እና ስነፍቺ በሚሉት አራት አበይት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመከፋፈል ያላቸውን የድግግሞሽ መጠን ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ የእነዚህን የሰዋስው ይዘቶች ልየታና አከፋፈል በተመለከተ ከአማካሪዬ በተጨማሪ የስራ ባልደረቦቼ የሆኑት የኢየሩሳሌም መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማረጋገጥ ስራ እንዲያከናውኑ ተደርጓል፡፡

## 4.2 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻህፍት ውስጥ በእያንዳንዳቸው 30 ምንባቦች ይገኛሉ፡፡ በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ምንባቦች እና የትምህርት ይዘቶች መሰረት ያደረጉ ተግባራት ተካተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከአማካሪዬ ጋር በመነጋገር በዚህ ጥናት በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሰዋስው በሚለው የትምህርት ዘርፍ ስር የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ወይም ተግባራት ብቻ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ የተግባራቱን የድግግሞሽ መጠን የመለየት ሂደቱም ከአንድ ጊዜ በላይ ድግግሞሽ ያላቸው ተመሳሳይ የሆኑ ተግባራት እንደአንድ ተግባር እንዲቆጠሩ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከተመረጡ ወይም ከተለዩ በኋላ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ምን ያህል የትኩረት ደረጃ እንደተሰጣቸው በሚከተለው መልክ ለማቅረብ ተችሏል፡፡

| ይዘት | በ7ኛ ክፍል | | በ8ኛ ክፍል | |
|---|---|---|---|---|
| | የድግግሞሽ መጠን | በመቶኛ | የድግግሞሽ መጠን | በመቶኛ |
| ስነድምጽ | --- | --- | --- | --- |
| ስነምእላድ | 10 | 35.7 | 13 | 41.9 |
| ስነአገባብ | 18 | 64.3 | 18 | 58.1 |
| ስነፍቺ | --- | --- | --- | --- |
| ድምር | 28 | 100 | 31 | 100 |

**ሰንጠረዥ 1፡-** በመማሪያ መጻህፍቱ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶችን የድግግሞሽ መጠን የሚያሳይ

ከላይ በሰንጠረዥ አንድ ላይ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ስነድምጽ እና ስነፍቺ ምንም አይነት ሽፋን ያላገኙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሲሆኑ፤ ስነምእላድ እና ስነአገባብ ደግሞ ሽፋን ያገኙ ይዘቶች ናቸው፡፡

በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት አጠቃላይ 28 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል ስነምእላድን መሰረት ያደረጉ ይዘቶች 10 ጊዜ (35.7 በመቶ) ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን፤ ስነአገባብን መሰረት ያደረጉ ይዘቶች ደግሞ 18 ጊዜ (64.3 በመቶ) ተደጋግው እናገኛቸዋለን፡፡ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ደግሞ ከቀረቡት አጠቃላይ 31 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል ስነምእላድን መሰረት ያደረጉ ይዘቶች 13 ጊዜ (41.9 በመቶ) ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን፤ በስነአገባብ ላይ ያተኮሩ ይዘቶች ደግሞ 18 ጊዜ (58.1 በመቶ) ተደጋግመው ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብዛት ተቀራራቢ ሲሆኑ፤ የስነአገባብ ይዘቶች በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ እኩል መጠን የተሰጣቸው እና ከሌሎቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለየ ከፍተኛ ትኩረት ያገኙ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ስነምእላድን እና ስነአገባብን ለማስተማር ከቀረቡ ተግባራት ወይም መመሪያዎች ውስጥ ለአብነት ያህል የተወሰኑትን ለማየት እንሞክራለን።

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ሰዋስው በሚለው የትምህርት ይዘት ስር ስነምእላድን ለማስተማር የቀረቡ ተግባራት ወይም መመሪያዎች በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ 10 ጊዜ የተደጋገሙ ሲሆን፤ ከእነዚህም ተግባራት መካከል በሚከተሉት አረፍተ ነገር ውስጥ ተውላጠ ስሞችን፣ ጾታን፣ መደብንና ቁጥርን መለየት፤ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች የአሁን፣ የሃላፊ እና የትንቢት ጊዜ በማለት መለየት፤ በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ተውሳከግሶችና ጊዜ አመልካቾች በመለየት አገልግሎታቸውን ግለጹ የሚሉት በገጽ 77፣ 189 እና 207 ላይ ቀርበዋል።

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ደግሞ 13 ጊዜ ተደጋግመው ይገኛሉ። ተግባራቱም የሚከተሉትን ቃላት በ2ኛ እና በ3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ቅርጻቸው እየለወጣችሁ ጻፉ፤ በቃላት እና በሀረጋት ውስጥ የሚገኙትን ጊዜ አመልካቾች ለዩ፤ ቃላትን በተለያየ ቅርጽ እያረባችሁ አዳዲስ ቃላትን መስርቱ፤ በ "ሀ" እና በ "ለ" ረድፍ የቀረቡት ቃላት የሚለዩባቸውን ቅርጾችና የቅርጾቹን አገልግሎት አብራሩ፤ የመሳሰሉት ሲሆኑ በገጽ 23፣ 60፣ 135 እና 176 ላይ ሰፍረዋል።

ስነአገባብን ለማስተማር የቀረቡት ተግባራት ደግሞ በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ 18 ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ሲሆን፤ በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚከተሉትን አያያዦች በትክክል በመጠቀም ጥንድ ጥንድ ሆነው የቀረቡትን ነጠላ አረፍተ ነገሮች ወደ ድርብ አረፍተ ነገር ለውጡ፤ ጠቋሚ መስተአምሮችንና ስምን እንደመሙያ የያዙ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፤ መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፤ ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን አሟልታችሁ ጻፉ በሚል በገጽ 20፣ 62፣ 102 እና 147 ላይ ቀርበዋል። በ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥም የሚከተሉትን አዎንታዊ አረፍተ ነገሮች ወደአሉታዊ አረፍተ ነገር ለውጡ፤ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ግሶቻቸው እንዳያስሩ በማድረግ ወደጥገኛ ሀረግ ለውጧቸው፤ ቀጥሎ የቀረቡትን ስማዊ ሀረጎች በመሙያነት በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፤ አዎንታዊ አረፍተ ነገሮችን ጽፋችሁ ወደአሉታዊ እና

መጠይቃዊ አረፍተ ነገር ቀይሩ፤ በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ጥገኛ ሀረጎች ለይታችሁ ጻፉ በሚል በገጽ 11፣ 77፣ 84፣ 127 እና 202 ላይ ሰፍረዋል፡፡

## 4.3 የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪ ፈተናዎቹ ውስጥ

በተተኳሪው ክልል በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. የተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች እያንዳንዳቸው 60 ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ የሁለቱ ፈተናዎች አደረጃጀት ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ከስድስት እስከ ሰባት በሚደርሱ መመሪያዎች የታቀፉ ሲሆን፤ መመሪያዎቹም በቋንቋ ክሂሎች፣ በሰዋስው፣ በስነጽሁፍ (በድርሰት)፣ ቀድሞ በቀረበው ምንባብ፣ በግጥም፣ በግራፍ እንዲሁም የቃላትንና የሀረጋትን (አውዳዊ፣ ተመሳሳይ እና ተቃራኒ) ፍቺ መስጠት ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱ ፈተናዎች ውስጥ ያሉት መመሪያዎች እና በመመሪያዎች ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ብዛት የተለያዩ ናቸው፡፡ ይኸውም በ2010 ዓ.ም. የቀረበው ክልላዊ ፈተና በውስጡ ስድስት መመሪያዎችን ያቀፈ ሲሆን፤ ቀድሞ የቀረበውን ምንባብ፣ የቃላትንና የሀረጋትን (አውዳዊ፣ተመሳሳይና ተቃራኒ) ፍቺ፣ ሰዋስውን፣ የቋንቋ ክሂሎችን፣ ቀድሞ የቀረበውን ግጥም እና ስነጽሁፍን (ድርሰትን) መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ባሉት መመሪያዎች ስር ቀርበዋል፡፡

በ2011 ዓ.ም. የቀረበው ክልላዊ ፈተና ደግሞ በውስጡ ሰባት መመሪያዎች ያሉት ሲሆን፤ የቃላትንና የሀረጋትን (አውዳዊ፣ተመሳሳይና ተቃራኒ) ፍቺ፣ ሰዋስውን፣ ቀድሞ የቀረበውን ምንባብ፣ ጽህፈትን፣ ቀድሞ የቀረበውን ግጥም፣ ቀድሞ የቀረበውን ግራፍ እና ቃላዊ ክሂሎችን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ባሉት መመሪያዎች ውስጥ ተካተዋል፡፡ ምንም እንኳን የጥያቄዎቹ ብዛት የተወሰኑ ቢሆኑም በሁለቱም ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ እነዚህም የሰዋስው ጥያቄዎች በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ በሶስተኛው መመሪያ ላይ “ሰዋስውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች” በሚል መመሪያ የቀረቡ ሲሆን፤ በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ደግሞ በሁለተኛው መመሪያ ላይ “ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች” ተብለው ቀርበዋል፡፡

ስለሆነም አጥኚው በተተኳሪ ፈተናዎቹ ውስጥ በሰዋስው ጥያቄዎች መመሪያ ስር የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ብቻ የጥናቱ አካል እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ የሰዋስው ጥያቄዎቹ በዚህ መልክ ከተለዩና ከተመረጡ በኋላ ለመመዘን እንደቀረቡበት የሰዋስው ትምህርት ዘርፍ ስነድምጽ፣ ስነምእላድ፣ ስነአገባብ እና ስነፍቺ በመባል በአራት ክፍሎች ተመድበው ብዛታቸው በሚቀጥለው ሰንጠረዥ በቁጥርና በመቶኛ ተገልጿል፡፡

| ይዘት | ክልላዊ ፈተናዎቹ የተሰጡበት አመተ ምህረት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2010 | | 2011 | |
| | ብዛት | በመቶኛ | ብዛት | በመቶኛ |
| ስነድምጽ | --- | --- | --- | --- |
| ስነምእላድ | 2 | 15.4 | 1 | 16.7 |
| ስነአገባብ | 8 | 61.5 | 4 | 66.7 |
| ስነፍቺ | 3 | 23.1 | 1 | 16.7 |
| ድምር | 13 | 100 | 6 | 100 |

**ሰንጠረዥ** 2፡- በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት የሚያሳይ

ከላይ በሰንጠረዥ ሁለት ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው አስራ ሶስት (13) እና ስድስት (6) የሰዋስው ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሰዋስው ጥያቄዎቹ በሁለቱም ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ አነስተኛ ሽፋን እንደተሰጣቸው ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ከሁለቱ ክልላዊ ፈተናዎች መካከል በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ የተሻለ ሽፋን እንዲያገኙ ሆነዋል፡፡

በ2010 ዓ.ም. በቀረበው ክልላዊ ፈተና ውስጥ ከተካተቱት አጠቃላይ 13 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ስነአገባብን በተመለከተ 8 ጥያቄዎች የቀረቡ በመሆኑ ስነአገባብ ከቀረቡት አበይት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች 61.5 በመቶ ሽፋን በማግኘት ከፍተኛውን ድርሻ እንዲይዝ ሆኗል፡፡ ስነፍቺን እና ስነምእላድን ለመፈተን ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው 3 እና 2

ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን፤ 23.1 በመቶ እና 15.4 በመቶ ሽፋን በማግኘት ሁለተኛውን እና ሶስተኛውን የትኩረት ደረጃ አግኝተዋል፡፡

በ2011 ዓ.ም. በቀረበው ክልላዊ ፈተና ውስጥ ደግሞ ከተካተቱት አጠቃላይ 6 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ስነአገባብን ለመፈተን 4 ጥያቄዎች የተካተቱ ሲሆን፤ 66.7 በመቶ ሽፋን በማግኘት የመጀመሪያውን የትኩረት ደረጃ ይዘዋል፡፡ ስነምእላድ እና ስነፍቺ ደግሞ እኩል ትኩረት ተሰጥቷቸው እያንዳንዳቸውን የትምህርት ይዘቶች በተመለከተ 16.7 በመቶ ሽፋን ያለው 1 ጥያቄ እንዲካተት ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ በፈተናው ውስጥ ስነምእላድ እና ስነፍቺ አነስተኛ ትኩረት እንደተሰጣቸው ያመለክታል፡፡

ስነድምጽን በተመለከተ ግን በሁለቱም አመታት በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ ምንም አይነት ጥያቄ ተካቶ አይገኝም፡፡ ይህ ደግሞ ልክ እንደ መማሪያ መጻህፍቱ ሁሉ በክልላዊ ፈተናዎቹም ውስጥ ሽፋን ያልተሰጣቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እንዳሉ ያስረዳል፡፡

ከዚህ በላይ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እና በክልላዊ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች መጠን ተናጠላዊ በሆነ መንገድ ለማየት ተሞክሯል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ በተተኳሪ ጥያቄዎቹ እና በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል ያለው የይዘት ተገቢነት ምን እንደሚመስል ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## 4.4 የመማሪያ መጻህፍቱ እና የሰዋስው ጥያቄዎቹ የይዘት ዝምድና

በምእራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው ፈተናዎች የይዘት ዝምድና ወይም ተገቢነት እንዲኖራቸው ሲዘጋጁ መሰረት በሚያደርጓቸው መርሃ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያሉትን የትምህርት ይዘቶች እንዲሁም የተሰጣቸውን የትኩረት ደረጃ መሰረት ማድረግ ይኖርባቸዋል (Finocchiaro and Brumfit 1983)፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ሰዋስውን ሲፈተኑ ለትምህርትነት የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ መሰረት ባደረገ መልኩ መሆን አለበት፡፡ ሰዋስው ደግሞ ስነድምጽን፣ ስነምእላድን፣ ስነአገባብን እና ስነፍቺን የሚያካትት ነው (Purpura 2004)፡፡ ይህ ደግሞ የሰዋስው ትምህርት ዘርፎች ስነድምጽ፣ ስነምእላድ፣ ስነአገባብ እና ስነፍቺ በመባል

በአራት አበይት ክፍሎች እንደሚከፈሉ እና በውስጣቸውም የተለያዩ ንኡሳን ይዘቶችን ያቀፉ እንደሆኑ ያስረዳል።

በዚህም መሰረት ቀጥሎ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች እና በተተኳሪው ክልል በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ያለውን የይዘት ዝምድና ለማሳየት በምእራፍ ሶስት ላይ ለመግለጽ እንደተገሞከረው የፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ቀመርን በመጠቀም ግልጽ በሆነ መልኩ ቀርበዋል። ይህንም ለማድረግ በቃለ መጠይቁ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ክልላዊ ፈተናዎቹ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎችን መማሪያ መጻህፍት ትኩረት በማድረግ በውስጣቸው ካሉት የትምህርት ይዘቶች መካከል ከእያንዳንዳቸው 50 በመቶ የሚሆኑትን ይዘቶች በመምረጥ በፈተናዎቹ ውስጥ እንዲካተቱ ሆነው ይዘጋጃሉ። ስለሆነም በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን አማካይ ውጤት በመውሰድ በፈተናዎቹ ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት ጋር በሰንጠረዥ ውስጥ ጎን ለጎን እንዲሰፍሩ ተደርጓል።

ለዚህም ያመቺ ዘንድ በሁለቱ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን አማካይ ውጤት በ “X” በክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት ደግሞ በ “Y” በመወከል በሰንጠረዥ በማስፈር በሁለቱ መካከል ያለውን ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ቀመር በማስላት ቀርቧል። በእያንዳንዱ ሰንጠረዥ ውስጥ የሰፈሩትን የአሃዝ መረጃዎች መሰረት ያደረጉ ትንታኔዎችም ከሰንጠረዡ ግርጌ ቀርበዋል።

| በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ይዘቶች | X | Y | $X^2$ | $Y^2$ | XY |
|---|---|---|---|---|---|
| ስነምእላድ | 11.5 | 2 | 132.3 | 4 | 23 |
| ስነአገባብ | 18 | 8 | 324 | 64 | 144 |
| ስነፍቺ | 0 | 3 | 0 | 9 | 0 |
| N= 3 | $\sum X$=29.5 | $\sum Y$=13 | $\sum X^2$=456.3 | $\sum Y^2$= 77 | $\sum XY$=167 |

**ሰንጠረዥ 3፡-** በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎችና የመማሪያ መጻህፍቱ ዝምድናን የሚያሳይ

$$r_{xy} = \frac{N\sum XY - \sum X \sum Y}{\sqrt{(N\sum X^2 - (\sum X)^2(N\sum Y^2 - (\sum Y)^2)}}$$

$$= \frac{3\times167 - 29.5\times13}{\sqrt{(3\times456.3 - (29.5)^2)(3\times77 - (13)^2}}$$

$$= \frac{501 - 383.5}{\sqrt{(1368.9 - 870.25)(231 - 169)}}$$

$$= \frac{117.5}{\sqrt{498.65\times139}}$$

$$= \frac{117.5}{\sqrt{30916.3}}$$

$$= 0.67$$

ያለው (2009፣340) በሁለት ተለዋዋጮች መካከል ያለው ተዛምዶ ከዜሮ ወደአንድ እየተጠጋ ወይም እቀረበ የሚሄድ ከሆነ የተለዋዋጮቹ ዝምድና ጠንካራና አዎንታዊ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ከላይ በሰንጠረዥ ሶስት ለማየት እንደተቻለው በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ያለው ዝምድና በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር እንደተረጋገጠው 0.67 ወይም 44.9 በመቶ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር መርህ መሰረት በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና በሰዋስው ጥያቄዎቹ መካከል ከፍተኛ እና ቀጥተኛ የሆነ ዝምድና እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱን መሰረት ያደረጉ እና አዎንታዊ የሆነ የይዘት ዝምድና አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ ከሰንጠረዥ አንድ እና ሁለት ለመረዳት እንደሚቻለው በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ "ሰዋስው" በሚለው የትምህርት ይዘት ስር ስነፍቺን በተመለከተ የቀረቡ ይዘቶች የሉም፡፡ በ2010 ዓ.ም በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ ግን "ሰዋስውን የተመለከቱ ጥያቄዎች" በሚለው መመሪያ ስር ስነፍቺን መሰረት ያደረጉ 3 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ይህ ደግሞ በፈተናው ውስጥ የተካተቱት ሁሉም የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ዝምድና እንደሌላቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ጥያቄዎቹም በፈተናው ውስጥ ከተካተቱት አጠቃላይ የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል 23.1 በመቶ ሽፋን አግኝተዋል፡፡ በጥያቄ ቁጥር 14፣ 15 እና 23 ላይ የሚገኙ ሲሆን በእማሬያዊ እና በፍካሬያዊ ፍቺ ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ይዘቶች ፈተናው ውስጥ ምንም አይነት ሽፋን እንዳላገኙ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ይዘቶች መካከል በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ተውላጠ ስሞች፣ ጾታ፣ መደብና ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን መለየት፤ በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ጊዜ አመልካቶች የአሁን፣ የሃላፊ እና የትንቢት ጊዜ በማለት መለየት፤ ቃላትን በአንደኛ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛ መደቦች ማርባት፤ በቃላትና በሀረጋት ውስጥ ያሉትን ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን መለየት፤ ቃላትን በተለያ ቅርጽ በማርባት አዳዲስ ቃላትን መመስረት፤ ቃላትን በቅርብ እና በሩቅ ሃላፊ ጊዜ ማርባት፤ አዎንታዊና

መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች፣ ጠቋሚ መስተአምሮች፣ ጥገኛ ሀረጎች፣ ስማዊ ሀረጎች የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ሌላው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍቱ እና በፈተናዎቹ ውስጥ የተሰጣቸው ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በ4.2 እና በ4.3 ንኡስ ርእስ ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሰፊ ሽፋን የተሰጣቸው ይዘቶች የተወሰኑ ጥያቄዎች እንዲወጣባቸው ተደርጓል፡፡ ይኸውም በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው 10 እና 13 ጊዜ ተደጋግመው በመቅረብ 35.4 እና 41.9 በመቶ ሽፋን የተሰጣቸው የስነምእላድ ይዘቶች በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ 15.4 በመቶ ሽፋን ባላቸው ሁለት ጥያቄዎች ተወክለው የቀረቡ ሲሆን፤ በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ውስጥ እኩል 18 ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ የስነአገባብ ይዘቶች ደግሞ በ8 ጥያቄዎች ብቻ ተወክለው ቀርበዋል፡፡ ተተኳሪ ጥያቄዎቹ ከሽፋን አንጻር ሲታዩ ተገቢነት እንደሌላቸው ያመለክታል፡፡

| በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች | X | Y | $X^2$ | $Y^2$ | XY |
|---|---|---|---|---|---|
| ስነምእላድ | 11.5 | 1 | 132.3 | 1 | 11.5 |
| ስነአገባብ | 18 | 4 | 324 | 16 | 72 |
| ስነፍቺ | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 |
| N= 3 | $\sum X$=29.5 | $\sum Y$= 6 | $\sum X^2$=456.3 | $\sum Y^2$=18 | $\sum XY$= 83.5 |

**ሰንጠረዥ 4፡-** በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎችና የመማሪያ መጻህፍቱ ዝምድናን የሚያሳይ

$$r_{xy}=\frac{N\sum XY-\sum X\sum Y}{\sqrt{(N\sum X^2-(\sum X)^2(N\sum Y^2-(\sum Y)^2)}}$$

$$=\frac{3\times83.5-29.5\times6}{\sqrt{(3\times456.3-(29.5)^2)(3\times18-(6)^2}}$$

$$=\frac{250-177}{\sqrt{(1368.9-870.25)(54-36)}}$$

$$=\frac{73}{\sqrt{498.65\times18}}$$

$$=\frac{73}{\sqrt{8975.7}}$$

$$=0.77$$

ከላይ በሰንጠረዥ አራት እንደተገለጸው በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ያለውን ዝምድና በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር መሰርት ለመፈተሽ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በሁለቱ መካከል ያለው ዝምድና 0.77 ወይም 59.3 በመቶ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ደግሞ በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ጋር ከፍተኛ እና አዎንታዊ የሆነ ዝምድና እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ ከሰንጠረዥ አንድ እና ሁለት ለመረዳት እንደሚቻለው በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ "ሰዋስው" በሚለው የትምህርት ይዘት ስር ስነፍቺን በተመለከተ የቀረቡ ይዘቶች የሉም፡፡ በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ ግን "ሰዋስውን የተመለከቱ ጥያቄዎች" በሚለው መመሪያ ስር ስነፍቺን መሰረት ያደረገ አንድ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ይህ ደግሞ ፈተናው ውስጥ የተካተቱት ሁሉም የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት ዝምድና እንደሌላቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ጥያቄ በፈተናው ውስጥ ከተካተቱ አጠቃላይ የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል 16.7 በመቶ ሽፋን ያገኘ ሲሆን፤ በጥያቄ ቁጥር 16 ላይ ቀርቧል፡፡ ጥያቄውም የአንድን አረፍተ ነገር ሀሳብ በሌላ ተመሳሳይ ሀሳብ መቀየር ላይ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ምንም አይነት ሽፋን እንዳላገኙ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ይዘቶች መካከል በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ተውላጠ ስሞች፣ ጾታ፣ መደብና ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን መለየት፤ በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ጊዜ አመልካቶች የአሁን፣ የሃላፊ እና የትንቢት ጊዜ በማለት መለየት፤ ቃላትን በአንደኛ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛ መደቦች ማርባት፤ በቃላትና በሀረጋት ውስጥ ያሉትን ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን መለየት፤ ቃላትን በተለያ ቅርጽ በማርባት አዳዲስ ቃላትን መመስረት፤ ቃላትን በቅርብ፣ በሩቅ ሃላፊ ጊዜ ማርባት፤ ተራ፣ ውስብስብ እና አዎንታዊ አረፍተ ነገሮች፣ ጥገኛ ሀረጎች፣ አያያዥ ቃላት፣ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ሌላው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍቱ እና በፈተናዎቹ ውስጥ የተሰጣቸው ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ሰፊ ሽፋን የተሰጣቸው ይዘቶች በተወሰኑ ጥያቄዎች እንዲወከሉ ተደርጓል፡፡ ይኸውም በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው 10 እና 13 ጊዜ ተደጋግመው በመቅረብ 35.4 እና 41.9 በመቶ ሽፋን የተሰጣቸው የስነምእላድ ይዘቶች በ2011 ዓ.ም በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ 16.7 በመቶ ሽፋን ባለው አንድ ጥያቄ ብቻ የተወከሉ ሲሆን፤ በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት እኩል 18 ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ የስነአገባብ ትምህርት ይዘቶች ደግሞ በ4 ጥያቄዎች ብቻ ተወክለው ቀርበዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በተሰጣቸው ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ መሰረት በፈተናዎቹ ውስጥ ውክልና አለማግኘታቸው ያመለክታል፡፡

የፈተና አዘጋጆች የፈተና አዘገጃጀትን በተመለከተ ስልጠና እንደሚውስዱ፣ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥን እንደሚጠቀሙ እና የተዘጋጁት ፈተናዎችም ከተፈታኝ ተማሪዎች ፊት ከመቅረባቸው በፊት በባለሙያዎች እንደሚገመገሙ በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክት ሲሆን፤ በሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አካላት አዎንታዊ የሆኑ ሀሳቦችን ብቻ እንደሰጡ ወይም የክልላዊ ፈተና አዘጋጆች ክልላዊ ፈተናዎችን በሚያዘጋጁበት ወቅት የፈተና አዘገጃጀት መርሆችን ሙሉ

በሙሉ ከግምት ውስጥ እንደማያስገቡ እና የተዘጋጁት ፈተናዎቹ በስርአቱ እንደማይገመገሙ የሚያመለክት ነው፡፡

በአጠቃላይ አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው በፈተናው ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በቀረቡት ይዘቶች ላይ የተመሰረቱ መሆን ብቻ ሳይሆን በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችን ሽፋን መሰረት አድርገው ሲዘጋጁም ጭምር ነው (Heaton 1975፣161)፡፡ ይሁን እንጂ በተተኳሪው ክልል በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ከፍተኛ እና አዎንታዊ የሆነ የይዘት ዝምድና ያላቸው ቢሆኑም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ መሰረት ያላደረጉ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ተተኳሪ የሰዋስው ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ የይዘት ተገቢነት አላቸው ለማለት የማያስደፍር መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

## 4.5 ከምርጫ ጥያቄዎች አቀራረብ መርህ አንጻር የተተኳሪ ጥያቄዎች አቀራረብ

በምእራፍ ሁለት ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ መሪ ጥያቄዎች ግልጽ እና ነጠላ ሀሳብን የያዙ እንዲሁም ጠቋሚ ሀሳቦችን ያልያዙ፤ አሳሳች (Distracters) ሆነው የገቡት አማራጮች ዋናውን መልስ የማሳሳት አቅም ያላቸው፤ ፍጹማዊ የሆኑ ቃላትን (ዘወትር፣ ፈጽሞ፣ አብዛኞቹ፣ ብቻ፣ የመሳሰሉ) ያልተጠቀሙ፤ በአንድ ጥያቄ ስር የሚቀርቡ ሁሉም አማራጮች ተመሳሳይ ይዘት፣ ቅርጽ እና አወቃቀር ያላቸው፤ ተያየዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ተከታትለው ያልቀረቡ፤ አላስፈላጊ የሆነ ድግግሞሽ የሌላቸው፤ የግል አስተያየትችን መሰረት ያላደረጉ፤ ሁሉም መልስ ናቸው፣ መልስ አልተሰጠም፣ ሀ እና ለ መልስ ናቸው፣ ወዘተ. የሚሉ አማራጮችን ያላካተቱ፤ አንድ መልስ ብቻ የያዘዙ ሊሆኑ ይገባል (Brown 1996)፡፡

በመሆኑም አጥኚው እነዚህን መርሆች መሰረት በማድረግ በተተኳሪ ክልላዊ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ ሁኔታ ፈትሿል፡፡ በፍተሻውም በሁለቱ ፈተናዎች ውስጥ ከተካተቱት 19 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል 11ዱ (57.9 በመቶ) የሚሆኑት ጥያቄዎች የአቀራረብ ችግር እንዳለባቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች ግልጽነት

የጎደላቸው፣ ወደ መልስ የሚያመራ ጠቋሚ ሀሳብ የያዙ፣ ደካማ የማሳሳት አቅም ያላቸው አማራጮችን የያዙ፣ ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ተከታትለው የቀረቡ እና አላስፈላጊ ድግግሞሽ ያለባቸው እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም አጥኚው እነዚህን የአቀራረብ ችግር ያለባቸውን ጥያቄዎች እንደሚከተለው በዝርዝር ለማቅረብ ሞክሯል፡፡

### ሀ. ከመሪ ጥያቄዎች ግልጽነት አንጻር

መሪ ጥያቄዎች ሊጠየቅ የተፈለገውን ጉዳይ በግልጽና በማያሻማ መንገድ ማቅረብ እንዳለባቸው የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከተካተቱት አጠቃላይ 13 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል 3ቱ (23.1 በመቶ) የሚሆኑት ጥያቄዎች ይህን መስፈርት ያላሟሉ ናቸው፡፡

**አስረጅ 1፡-**

19. ቀጥሎ ከቀረቡት ውስጥ ስህተት ያለበት አጻጻፍ የቱ ነው? (2010 ዓ.ም.)

A. የሀይሉ እህት አገባች፡፡ C. ረጅሙን ዛፍ ቆረጡት፡፡

B. ይህ ጫማ ተውና ያ አድርግ፡፡ D. ሻዩ ውስጥ ብዙ ስኳር አለበት፡፡

23. "ሀሜሶ ትምህርቱን ጨርሶ እንጀራ ወጣለት፡፡" የሚለው ዓረፍተ ነገር የተጻፈው ከሚከተሉት በየትኛው አጻጻፍ ነው? (2010 ዓ.ም.)

A. ምንባብ C. ግጥም

B. ፍካሬያዊ D. ሀረግ

25. ሱራፌል ከአዲስ አበባ ዛሬ <u>**ወይም**</u> ነገ ይገባል፡፡ የተሰመረበት ቃል የሚያመለክተው የቱ ነው? (2010 ዓ.ም.)

A. አያያዥ C. አነጻጻሪ

B. መስተዋድድ D.ገላጭ

(አባሪ አንድን ይመልከቱ)

ከላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ በጥያቄ ቁጥር 19፣ 23 እና 25 ላይ ተካተው የሚገኙ ሲሆን፤ መሪ ጥያቄዎቻቸው ሊጠየቅ የተፈለገውን ጉዳይ በግልጽ የማቅረብ ችግር ይስተዋልባቸዋል፡፡ ይኸውም በጥያቄ ቁጥር 19 ላይ "ቀጥሎ ከቀረቡት ውስጥ ስህተት ያለበት አጻጻፍ የቱ ነው?" ተብሎ የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎቹ የሰዋስው ስህተት ያለበትን አረፍተ ነገር እንዲለዩ ለማድረግ የቀረበ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጥያቄው አቀራረብ የአጻጻፍ ስርአትን ወይም የስርአተ ነጥብን አጠቃቀም መሰረት ያደረገ ስለሚመስል አሻሚነት አለው፡፡ በመሆኑም መሪው ጥያቄ "ቀጥሎ ከቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሰዋስው ስህተት ያለበት የትኛው ነው?" ተብሎ ቢጠየቅ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡

ሌላው በጥያቄ ቁጥር 23 ላይ የቀረበው ጥያቄ "ሀሜሶ ትምህርቱን ጨርሶ እንጀራ ወጣለት፡፡" የሚለው አረፍተ ነገር "ሀሜሶ ትምህርቱን በመጨረሱ አለፈለት" የሚል መልእክት የሚኖረው መቼ እንደሆነ ለመግለጽ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡ ነገር ግን የጥያቄው አቀራረብ የአጻጻፍ ስልትን እንጂ አረፍተ ነገሩ የሚያስተላልፈውን መልእክት የሚጠይቅ አይመስልም፡፡ ስለሆነም "ሀሜሶ ትምህርቱን ጨርሶ <u>እንጀራ ወጣለት</u>፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ሀረግ (ፈሊጣዊ አነጋገር) ምን አይነት ፍቺ አለው? ተብሎ ቢቀርብ የበለጠ ግልጽ ይሆን ነበር፡፡ ይህ እንኳን ባይሆን በስሩ የተካተቱት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ የመምሰል ወይም የማሳሳት አቅም ያላቸው እና ከፍቺ ጋር የተየያዙ ሆነው ቢቀርቡ ጥሩ ነበር፡፡

እንዲሁም በጥያቄ ቁጥር 25 ላይ "ሱራፌል ከአዲስ አበባ ዛሬ **<u>ወይም</u>** ነገ ይገባል፡፡ የተሰመረበት ቃል የሚያመለክተው የቱ ነው?" በሚል የቀረበው መሪ ጥያቄ ሊጠየቅ የተፈለገውን ጉዳይ በግልጽ አያሳይም፡፡ ስለሆነም "ሱራፌል ከአዲስ አበባ ዛሬ **<u>ወይም</u>** ነገ ይገባል፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አገልግሎት ምንድን ነው?" ተብሎ ቢጠየቅ የተሻለ ያደርገዋል፡፡

**ለ. መሪ ጥያቄዎች ጠቋሚ ሀሳብን ያልያዙ ከመሆናቸው አንጻር**

መሪ ጥያቄዎች ወደ መልስ ሊያመሩ የሚችሉ ጠቋሚ ሀሳቦችን ማካተት እንደሌለባቸው በምእራፍ ሁለት ላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች መሪ ጥያቄዎቻቸው ወደመልስ የሚያመሩ ጠቋሚ ሀሳቦችን የያዙ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ፍተሻ አብዛኞቹ የተሻሉ ቢሆኑም በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ ከተካተቱት አጠቃላይ 6 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል 16.7 በመቶ ሽፋን የተሰጠው አንድ ጥያቄ ይህን መስፈርት መሰረት ያላደረገ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**አስረጅ 2፡-**

11. ለሰዎች ወይም ለነገሮች መጠሪያ (ስያሜ) በመሆን የሚያገለግል የቃል ክፍል ..............

በመባል ይታወቃል፡፡ (2011 ዓ.ም.)

A. ቅጽል　　　C. ስም

B. ግስ　　　D. መስተዋድድ (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)

ከምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች አቀራረብ መርሆች ውስጥ አንዱ አንድ መሪ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቁሙ ሀሳቦችን ማካተት የለበትም የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ በጥያቄ ቁጥር 11 ላይ በሚገኘው ጥያቄ ውስጥ የተካተቱት “መጠሪያ (ስያሜ)” የሚሉት ቃላት ለትክክለኛው መልስ ፍንጭ ሰጪ ናቸው፡፡ ስለሆነም “መጠሪያ (ስያሜ)” የሚሉትን ቃላት መነሻ በማድረግ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛው መልስ የትኛው እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥያቄ አቀራረብ አንድ መሪ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቁሙ ሀሳቦች ማካተት የለበትም የሚለውን መርህ ተግባራዊ ስላላደረገ ችግር አለበት ማለት ይቻላል፡፡

### ሐ. መልስ የሚመስሉ አሳሳች አማራጮችን ከማቅረብ አንጻር

በምርጫ ጥያቄ አቀራረብ ስልት በአንድ ጥያቄ ስር የሚቀርቡ አሳሳች አማራጮች ለጥያቄው መልስ ከሆነው አማራጭ ጋር በቅርጽ እና በክብደት ደረጃ ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ወይም ትክክለኛውን መልስ በቀላሉ ለመምረጥ በሚያዳግት ሁኔታ መቅረብ ይገባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም አሳሳች አማራጮች ለጥያቄው መልስ ከሆነው አማራጭ ጋር በቅርጽ እና በይዘት ከተመሳሰሉ ተፈታኝ ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ በቀላሉ የሚለዩት ሳይሆን በደንብ እንዲያስቡና እንዲመረምሩ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡

ይሁን እንጂ በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከተካተቱት 13 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል 2 (15.4 በመቶ) እንዲሁም በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከተካተቱት 6 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ደግሞ 2 (33.3 በመቶ) ጥያቄዎች ስር የቀረቡት አሳሳች አማራጮች የማሳሳት አቅማቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

**አስረጅ 3፡-**

13. ከሚከተሉት **ትእዛዛዊ** አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው? (2010 ዓ.ም.)

A. ወደ ቤት አልሄድም፡፡ C. አየለ መቼ ትመጣለህ?

B. አየለ ምሳህን ብላ፡፡ D. አየለ ምን በላህ?

15. "**እርግብ**" ለሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቺ የቱ ነው? (2010ዓ.ም.)

A. የዋህ C. ድሀ

B. ንፉግ D. የወፍ ዝርያ

13. "አለሙ ምሳውን በላ፡፡" የሚለው አረፍተ ነገር ወደ አሉታዊ አረፍተ ነገር ሲቀየር ---------- ይሆናል፡፡ (2011 ዓ.ም.)

A. አለሙ ምስውን ይብላ፡፡ C. አለሙ ምሳውን አልበላም፡፡

B. አለሙ ምሳውን በልቷል፡፡ D. አለሙ ምሳውን መቼ በላ?

14. እነዚያ የታቦርና የአላሙራ ተራሮች ለሀዋሳ ከተማ ሞገስ ሆነዋታል፡፡ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ጠቋሚ መስተኣምሩ ማነው? (2011 ዓ.ም.)

A. ሞገስ C. ተራሮች

B. እነዚያ D. ሀዋሳ ከተማ

(አባሪ አንድን እና ሁለትን ይመልከቱ)

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በ2010 ዓ.ም. በጥያቄ ቁጥር 13 እና 15 ላይ በቀረቡት መሪ ጥያቄዎች ስር የተዘረዘሩት አሳሳች አማራጮች የማሳሳት አቅማቸው ደካማ ነው፡፡ ይኸውም በጥያቄ ቁጥር 13 ላይ በቀረበው መሪ ጥያቄ ስር አማራጭ C እና D በጥያቄ ምልክት ስለተጠናቀቁ መጠይቃዊ እንጂ ትእዛዛዊ አረፍተ ነገሮች እንዳልሆኑ በቀላሉ መለየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የዚህን ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለማወቅ የሚያስፈልገው አማራጭ Aን እና Bን ማነጻጸር ብቻ ነው ፡፡ ይህ ደግሞ በአሳሳችነት የቀረቡት አማራጮች ዋናውን መልስ የመምሰል አቅማቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በጥያቄ ቁጥር 15 ላይ የቀረበው ጥያቄ ደግሞ በቃላት እማሬያዊ ወይም ቀጥተኛ ፍቺ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ በስሩ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ሶስቱ ማለትም አማራጭ A፣ B እና C ቃላት ከመሆናቸው በተጨማሪ ከቃል ክፍሎች መካከል በቅጽል የቃል ክፍል ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ አማራጫ D ግን ሀረግ ሲሆን የቃል ክፍሉም ቅጽል አይደለም፡፡ ይህ ልዩ የሆነው አማራጭ ደግሞ የጥያቄው መልስ በመሆኑ ምክንያት የጥያቄውን መልስ አላስፈላጊ የሆነ ጥቆማ ይሰጣል፡፡ በመሆኑም ጥያቄው ጠንካራ አሳሳቾችን ከማቅረብ አንጻር ድክመት ይታይበታል፡፡

ሌላው በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ በጥያቄ ቁጥር 13 እና 14 ላይ በቀረቡት መሪ ጥያቄዎች ስር የተዘረዘሩት አሳሳች አማራጮች የማሳሳት አቅማቸው አናሳ ነው፡፡ በመሆኑም በጥያቄ ቁጥር 13 ላይ በቀረበው መሪ ጥያቄ ስር አማራጮች C በጥያቄ ምልክት ስለተጠናቀቀ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር መሆኑን በቀላሉ መለየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የዚህን ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለመምረጥ የሚያስፈልገው አማራጭ A፣ B እና Dን ማነጻጸር ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህም አማራጮች መካከል ደግሞ በአማራጭ A በቀረበው አረፍተ ነገር ውስጥ እንደማሰሪያ አንቀጽ ሆኖ የገባው ግስ አሉታ አመልካች ቅጥያ ያለበት ሲሆን፤ በአማራጭ B እና D በቀረቡት አረፍተ ነገሮች እንደማሰሪያ አንቀጽ ሆነው በገቡት ግሶች ላይ ምንም አይነት አሉታ አመልካች ቅጥያዎች አይገኙም፡፡ ስለዚህ ከተሰጡት አማራጮች መካከል አሉታዊ አረፍተ ነገርን የያዘው አማራጭ A እንደሆነ በቀላሉ መለየት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ አሳሳች አማራጮች ዋናውን መልስ የመምሰል አቅም እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

በጥያቄ ቁጥር 14 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ አሳሳች ሆነው የቀረቡት አማራጮች ማለትም አማራጭ A እና C ስሞች ሲሆኑ አማራጭ D ደግሞ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ በመሆኑም ስሞች (የተጸእዎ እና የወል ስሞች) እንዲሁም ስማዊ ሀረጎች ጠቋሚ መስተኣምር ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ አማራጭ C መሆኑን መገመት ከባድ አይሆንም፡፡

**መ. የሀሳብ ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ተከታትለው ከመቅረባቸው አንጻር**

በአንድ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ ጥያቄዎች ቀድመዋቸው ወይም ተከትለዋቸው ከሚቀርቡት ጥያቄዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሆን እንደሌለባቸው የመስኩ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ይሁን እንጂ በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከተካተቱት 13 የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል 2ቱ (15.4 በመቶ) የሚሆኑት ይህን መርህ መሰረት ያላደረጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**አስረጅ 4፡-**

16. ቀጥሎ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ **በተራ** ዓረፍተነገር የተገለጸው የቱ ነው? (2010 ዓ.ም.)

A. ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ወጡ፡፡ C. ሰራተኞች ገንዘባቸውን ስለጨረሱ ተቸገሩ፡፡

B. ለማ ቁርሱን በልቶ ወደ ገበያ ሄደ፡፡ D. አባቱ በመምጣቱ ደስ አለው፡፡

17. ከሚከተሉት ውስጥ **ውስብስብ** ዓረፍተ ነገር የሆነው የትኛው ነው? (2010 ዓ.ም.)

A. አበበ እራሱን ስለ አመመው ወደ ሀኪም ቤት ሄደ፡፡ C. ገበሬው ማሳውን አጠረ፡፡

B. ጥበቃው በሩን ዘጋው፡፡ D. ሰፈራቸውን በህብረት አጸዱ፡፡

(አባሪ አንድን ይመልከቱ)

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና በጥያቄ ቁጥር 16 እና 17 ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን መለየት ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ጌታሁን (2011) እንደሚገልጹት ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ለመለየት ዋናው መስፈርት በውስጣቸው የያዙትን የግስ ብዛት መሰረት ማድረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም አንድ ተማሪ የተራ አረፍተ ነገርን መዋቅር ለየ ወይም አወቀ ማለት በተዘዋዋሪ የውስብስብ አረፍተ ነገርን መዋቅር መለየት ይችላል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ጥያቄዎቹ ተያያዥነት እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በአንድ ፈተና ውስጥ ተከታትለው መቅረብ እንደሌለባቸው የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም የሁለቱ ጥያቄዎች አቀራረብ ከዚህ መስፈርት አንጻር ሲታዩ ችግር እንዳለባቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በጥያቄ ቁጥር 17 ስር የቀረቡትን አማራጮች ቅርጻዊ መዋቅር ስናይ አማራጭ A ከሌሎች አማራጮች በተለየ መልኩ ረዘም ብሎ ይታያል፡፡ ይህ ልዩ የሆነው አማራጭ ደግሞ የጥያቄው መልስ በመሆኑ ምክንያት የጥያቄውን ትክክለኛ መልስ ይጠቁማል፡፡ ስለሆነም በጥያቄው ስር የቀረቡት አሳሳች አማራጮች የማሳሳት አቅማቸውም ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### ሠ. ከአላስፈላጊ ድግግሞሽ አንጻር

የፈተና ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ወቅት አላስፈላጊ ከሆኑ የቃላት ድግግሞሽ የጸዱ መሆን እንዳለባቸው የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከተተኳሪ ጥያቄዎች ውስጥ በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና 7.7 በመቶ ሽፋን ያለው አንድ ጥያቄ ይህን መስፈርት እንዳላሟላ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**አስረጅ 5፡-**

24. ወንድሜ <u>ገና</u> አልመጣም፡፡ የተሰመረበት ቃል ከሚከተሉት የትኛውን ያመለክታል? (2010 ዓ.ም)

A. ሁኔታን አመልካች C. ጊዜን አመልካች

B. ቦታን አመልካች D. ብዛትን አመልካች (አባሪ አንድን ይመልከቱ)

በዚህ ጥያቄ ስር በቀረቡት አራቱም አማራጮች ውስጥ "አመልካች" የሚለው ቃል ተደጋግሞ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ በመሪ ጥያቄው ውስጥ "ያመለክታል" የሚል ቃል ስላለ በአማራጮቹ ላይ የሚታየው ድግግሞሽ አላስፈላጊ ከመሆኑ ባሻገር የተፈታኝ ተማሪዎችን ጊዜ ይሻማል፡፡ ስለሆነም ጥያቄው "ወንድሜ <u>ገና</u> አልመጣም፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ከሚከተሉት የትኛውን ያመለክታል? A. ሁኔታን B. ቦታን C. ጊዜን D. ብዛትን" በሚል መንገድ ቢቀርብ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡

በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የፈተና አዘጋጆች የፈተና አዘገጃጀትን በተመለከተ ስልጠና እንደሚውስዱ እና የተዘጋጁት ፈተናዎችም ከተፈታኝ ተማሪዎች ፊት ከመቅረባቸው በፊት በባለሙያዎች እንደሚገመገሙ ቢያመለክትም በሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚቃረን እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አካላት አዎንታዊ የሆኑ ሀሳቦችን ብቻ እንደሰጡ ወይም የክልላዊ ፈተና አዘጋጆች ክልላዊ ፈተናዎችን

በሚያዘጋጁበት ወቅት የፈተና አዘገጃጀት መርሆችን ሙሉ በሙሉ ከግምት ውስጥ እንደማያስገቡ እና የተዘጋጁት ፈተናዎቹ በስርአቱ እንደማይገመገሙ የሚያመለክት ነው፡፡

በአጠቃላይ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት አጠቃላይ 19 የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ ከምርጫ ጥያቄዎች አቀራረብ መርህ አንጻር ሲፈተሹ 11ዱ (57.9 በመቶ) የሚሆኑት ጥያቄዎች ችግር ያለባቸው፤ 8ቱ (42.1 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ አንጻራዊ በሆነ መልኩ የአቀራረብ መርሆችን መሰረት ያደረጉ እንደሆኑ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይኸውም በ2010 ዓ.ም በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከተካተቱ አጠቃላይ 13 የሰዋስው ጥያቄዎች መሪ ጥያቄዎቻቸው በግልጽ ያልቀረቡ 3 (23.1 በመቶ) ጥያቄዎች፣ የማሳሳት አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ አማራጮችን የያዙ 2 (15.4 በመቶ) ጥያቄዎች፣ ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ተከታትለው የቀረቡ 2 (15.4 በመቶ) እና አላስፈላጊ የሆነ ድግግሞሽ ያለበት 1 (7.7 በመቶ) ጥያቄ እንዲሁም በ2011 ዓ.ም በተሰጠው ፈተና ውስጥ ደግሞ አላስፈላጊ ጥቆማን የሚሰጥ 1 (16.7 በመቶ) ጥያቄ እና የማሳሳት አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ አማራጮችን የያዙ 2 (33.3 በመቶ) ጥያቄዎች እንዳሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአንጻሩ ፍጹማዊ ቃላትን ካለመጠቀም፣ አንድ መልስ ብቻ ከመያዝ፣ ሁሉም መልስ ናቸው፣ መልስአልተሰጠም፣ ሀ እና ለ መልስ ናቸው፣ የመሳሰሉትን አማራጮች ካለመያዝ አንጻር ጠንካራ ጎን እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተተኳሪው ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ደካማ ጎናቸው የጎላ ቢሆንም ጠንካራ ጎንም አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

# ምእራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳው አላማ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ሲሆን በስሩ ሶስት ንኡሳን አላማዎችን ይዟል፡፡ እነዚህም አላማዎች ከግብ ለማድረስ ያመቺ ዘንድ አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ መረጃዎቹም በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡

በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በተተኳሪ መርሃ ትምህርቶቹ እና መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተመሳሳይ መሆናቸው ስለተረጋገጠ የተተኳሪ ጥያቄዎችን የይዘት ተገቢነት ለመፈተሽ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ በመሆኑም በተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ በተተኳሪ ፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች እና በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስነድምጽ፣ ስነምእላድ፣ ስነአገባብ እና ስነፍቺ በመባል ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ በዚህ መሰረት በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ያላቸውን ዝምድና በተመለከተ የተገኙ መረጃዎችን በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር በማስላት ወደመቶኛ ተቀይረው ሲቀርቡ የጥያቄዎችን አቀራረብ በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በቁጥርና በመቶኛ ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን፤ የሚከተለውን ውጤት ለማግኘት ተችሏል፡፡

**የይዘት ዝምድናን በተመለከተ**

- በተተኳሪው ክልል በ2010 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ በተካተቱ በሰዋስው ጥያቄዎች እና በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ መካከል ያለውን ዝምድና በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር በመፈተሽ የተገኘውም ውጤት 0.67 ወይም 44.9 በመቶ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር ህግ መሰረት በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና የሰዋስው ጥያቄዎቹ መካከል ያለው ተዛምዶ ከፍተኛ እና አዎንታዊ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡
- በ2011 ዓ.ም. በተሰጠው ክልላዊ ፈተና ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች እና በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ መካከል ያለውን ዝምድና በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር በመፈተሽ የተገኘውም ውጤት 0.77 ወይም 59.3 በመቶ ነው፡፡ ይህ ማለት በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ እና በሰዋስው ጥያቄዎቹ መካከል ያለው ተዛምዶ ከፍተኛ እና አዎንታዊ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል አብዛኞቹ ከተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ጋር ከፍተኛና አዎንታዊ የሆነ የይዘት ዝምድና ያላቸው ቢሆኑም የተወሰኑ ጥያቄዎች ግን ከመማሪያ መጻህፍቱ ጋር ዝምድና እንደሌላቸው በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ውክልና በተመለከተ**

በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ መሰረት ያደረጉ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ፍተሻ ጥያቄዎቹ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ለቀረቡት ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ወካይ ሆነው አልተገኙም፡፡ ምክንያቱም በፈተናዎቹ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉት ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል በጣም ጥቂቶቹ እንደሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶችም ቢሆኑ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተሰጣቸውን ሽፋን ወይም

የትኩረት ደረጃ መሰረት ያላደረጉ ሆነው ተገኝተዋል። ይህ ደግሞ ተተኳሪ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ የይዘት ተገቢነት አላቸው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ያደርገዋል።

**የጥያቄዎቹን አቀራረብ በተመለከተ**

በሁለቱም ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎችን አቀራረብ መርሆች ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን ለመፈተሽ በተደረገው ሙከራ የአብዛኞቹ ጥያቄዎች ደካማ ጎናቸው የሚያመዝን ቢሆንም ጠንካራ ጎንም እንዳላቸው በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይኸውም በ2010 ዓ.ም. እና በ2011 ዓ.ም. በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው 8 (61.5 በመቶ) እና 3 (50 በመቶ) የሚሆኑት ጥያቄዎች የአቀራረብ ችግር ያለባቸው ሲሆን፤ 5 (38.5 በመቶ) እና 3 (50 በመቶ) የሚሆኑት ጥያቄዎች ደግሞ በአንጻራዊነት የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎችን የአቀራረብ መርህ ተከትለው የቀረቡ እንደሆኑ ተረጋግጧል። በአጠቃላይ ተተኳሪ ጥያቄዎች ውስጥ መሪ ጥያቄዎቻቸው በግልጽ ያልቀረቡ፣ አላስፈላጊ ጥቆማን የሚሰጡ፣ የማሳሳት አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ አማራጮችን የያዙ እና አላስፈላጊ የሆነ ድግግሞሽ ያለባቸው ጥያቄዎች መካተታቸው የጥያቄዎቹን ደካማ ጎን የሚያሳይ ሲሆን፤ በአንጻሩ ፍጹማዊ ቃላትን፣ ከአንድ በላይ የሆኑ መልሶችን፣ ሁሉም መልስ ናቸው፣ መልስ አልተሰጠም፣ ሀ እና ለ መልስ ናቸው፣ የመሳሰሉትን አማራጮች ያላካተቱ መሆናቸው ደግሞ ጠንካራ ጎናቸውን ያመለክታል።

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

የዚህ ጥናት አድራጊ በጥናቱ የደረሰበትን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች አቅርቧል።

- ክልላዊ ፈተናዎች በባህሪያቸው አንድ መርሃ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሰጡ በመሆናቸው ሲዘጋጁ መሰረት በሚያደርጓቸው ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የቀረቡ ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች እንደተሰጣቸው የሽፋን መጠን ማካተት እንዳለባቸው ይታመናል። ይሁን እንጂ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በተተኳሪ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ የሰዋስው ጥያቄዎች በተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ምንም

አይነት ሽፋን እንዳልተሰጣቸው እና የተካተቱም የሰዋስው ጥያቄዎች ቢሆኑ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተሰጣቸውን ሽፋን ወይም የትኩረት ደረጃ መሰረት ያላደረጉ እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል። ይህ ችግር ደግሞ የፈተና ጥያቄዎች ሲዘጋጁ መሰረት በሚያደርጓቸው ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የቀረቡ አቢይ እና ንኡስ ይዘቶችን በተገቢው ሁኔታ ካለመፈተሽ የሚመነጭ ነው። በመሆኑም ወደፊት በሚዘጋጁ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ሁሉም ይዘቶች እንዲካተቱ እና መሰረት በሚያደርጓቸው ማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ ከተሰጣቸው ሽፋን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና እንዲኖራቸው ለማድረግ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን እንደሚመክሩት ክልላዊ ፈተናዎችን የሚያዘጋጁ አካላት ጥያቄዎችን ሲያዘጋጁ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥን (Tabel of Specification) በስርአቱ ቢጠቀሙ የተሻለ ይሆናል።

- የጥያቄዎችን አቀራረብ በተመለከተ ደግሞ ክልላዊ ፈተናዎች በምርጫ መልክ የሚቀርቡ በመሆናቸው የምርጫ ሰጪ ጥያቄ አቀራረብ መርሆችን መሰረት አድርገው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተተኳሪ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ የሰዋስው ጥያቄዎች የአቀራረብ ችግር እንዳለባቸው ጥናቱ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የክልላዊ ፈተና አዘጋጆች ወደፊት ጥያቄዎችን በሚያዘጋጁበት ወቅት የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎችን የአቀራረብ መርሆች መሰረት ቢያደርጉ ጥሩ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የታዩ ችግሮች ወደፊት በሚዘጋጁ ክልላዊ ፈተናዎች ላይ እንዳይደገሙ ለማድረግ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥን (Tabel of Specification) ከመጠቀም እና የምርጫ ሰጪ ጥያቄ አቀራረብ መርሆችን መሰረት ከማድረግ በተጨማሪ ከእስካሁኑ በተሻለ ሁኔታ በየአመቱ ክልላዊ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት ለሚመረጡ የትምህርት ባለሙያዎች ወይም መምህራን ከፈተና ዝግጅት በፊት ስለፈተና አዘገጃጀት ስልጠና ቢሰጥ፤ ከፈተና ዝግጅቱም በኋላ ፈተናው ወደተማሪዎች ከመድረሱ በፊት የተዘጋጁት ጥያቄዎች ተማሪዎች ከተማሩት የትምህርት ይዘት እና ለፈተናዎቹ ዝግጅት መሰረት ከሆኑት ማስተማሪያ መሳሪያዎች ጋር ተመጣጣኝ የትኩረት ደረጃ ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን እየተገመገሙ ማስተካከያዎች ቢደረጉ የፈተናዎቹን ችግር በመቅረፍ የተሻሉ ፈተናዎችን ማዘጋጀት እንደሚቻል አጥኚው ያምናል፡፡

# ዋቢዎች

መሰረት አለማየሁ፡፡ 2005 ዓ.ም፡፡ “በትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው ከ1999 እስከ 2004 ዓ.ም በተሰጡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ፡፡” ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ሙሉጸሀይ ገነት፡፡ 2005 ዓ.ም፡፡ “ከ2001- 2004 ዓ.ም በተሰጡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሞዴል እና ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ በቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ያለ የይዘት የአቀራረብ ዝምድና በአማራ ክልል ት/ቤቶች ናሙናነት፡፡” ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ ስርአተ ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር መምሪያ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ *አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ 7ኛ ክፍል፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡

----- 2007 ዓ.ም፡፡ *አማርኛ የመምህሩ መምሪያ መጽሀፍ 7ኛ ክፍል፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡

----- 2007 ዓ.ም፡፡ *አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ 8ኛ ክፍል፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡

------ 2007 ዓ.ም፡፡ *አማርኛ መምህሩ መምሪያ መጽሀፍ 8ኛ ክፍል፡፡* አዲስ አበባ፣

አርቲስቲክ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፡፡

ባየ ይማም፡፡ 1987 ዓ.ም፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ተስፋዬ ሽዋዬ፡፡ 1981 ዓ.ም፡፡ "ስነልሳን እና ቋንቋን ማስተማር፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

አበበች ገብሩ፡፡ 2004 ዓ.ም፡፡ "ከ1998 እስከ 2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ አማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ፡፡" ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ኤልሳቤጥ መንግስቱ፡፡ 2009 ዓ.ም፡፡ "ከ2004- 2007 ዓ.ም የተሰጡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ከሞዴል ፈተናዎች ጋር ያላቸውን የይዘት አቀራረብ ንጽጽር (በአፋር ክልል በዱቡቲ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት)፡፡" ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

የትምወርቅ ዘውዴ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ "ከ2004- 2006 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ተዘጋጅቶ የ8ኛ ክፍል የቀረበው *የአማርኛ ቋንቋ የ*ሞዴል ፈተና ከክልላዊ ፈተና ጋር ያለው ተዛምዶ እና የይዘት ተገቢነት ፍተሻ፡፡" ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ 2009 ዓ.ም፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡* መደበኛ፣

ድህረታዊ፣ መጣኝ፡፡ አዲስ አበባ፤ ኦሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ዳንኤል ዘውዴ፡፡ 2006 ዓ.ም፡፡ *በክፍል ምዘና አተገባበር ተጨባጭ ስልቶች፡፡* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ 2011 ዓ.ም፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡* አዲስ አበባ፤ (2ኛ እትም) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢ.ኢ. ማተሚያ ቤት፡፡

Alderson, J. C., Clapham, C. and Wall, D. 1995. *Language Test Construction and Evaluation.* Cambridge: Cambridge University Press.

Bachman, L. F. 1990*. Fundamental Consideration in Language Testing.* Oxford University Press.

Baker, D. 1989. *Language Testing: A Critical Survey and Practical Gide.* London: Edward Arnolds.

Best, J. W. and Khan, J. V. 2002. *Research in Education.* New Delhi: Prentice Hall of India.

Brown, J. D. 1994. *Principles of Language Learning and Teaching.* New Jersy: Prentice Hall Regents.

-------- 1996. *Testing in Language Programs.* New Jersy: Prentice Hall Regents.

Carroll, B. J. 1990. *Testing Communicative Performance.* Oxford: Pergamon Press Ltd.

Davies, A. 2001. *Studies in Language Testing.* Cambridge: Cambridge University Press.

Dornyei, Z. 2007. *Research Methods in Applied Linguistics.* Oxford: Oxford University Press.

Finocchiaro, M. and Brumfit, C. 1983. *The Fundamental National Approach: From Theory to Practice.* Oxford: Oxford University Press.

Fulcher and Davidson. 2007. *Language Testing and Assessment.* New York: Routletedge.

Gronlund, E, N. 1981. *Measurement and Evaluation in Teaching.* Macmillan Pulishing. Co.INC, New York.

--------- 1988. *How to Construct Achievement Tests.* New Jersey: Prentice Hall Inc.

Harrison, A. 1983. *A Language Testing Handbook.* London: Macmillan Pulishers.

Heaton,J. B. 1975. *Writing English Language Tests.* London: Longman.

--------- 1990. *Classroom Testing.* London: Longman. Group Ltd.

Hughes, A. 1989. *Testing for Language Teachers.* Cambridge: Cambridge University Press.

Kitao, S.K. and Kitao, K. 1996. *Testing Grammar.* Internationa Journal,2,6.

Kopriva, R. 2008. *Improving for Language Learners.* New York: Routletedge.

Madson, H, S. 1983. *Teachinques in Testing.* New York: Oxford University Press.

Purpura, J. E. 2004. *Assessing Grammar.* Cambridge: Cambridge University Press.

Weir, C, J. 1993. *Understanding and Developing Tests.* London: Parentice Hall.

--------- 2005. *Language Testing and Validation.* New York: Palgrave Macmillan.

# አባሪ አንድ

**የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ /8ኛ ክፍል/ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና**

**የጥያቄ ብዛት፡- 60**

**የተሰጠው ሰዓት 60 ደቂቃ**

**ሰኔ 2010/2018**

***መመሪያ*** **አንድ፡-** ከተራ ቁጥር 1እስከ5 ድረስ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ጪ፡፡

**ምንባብ**

ሰላም <u>የህይወት ዋስትና</u> ነው፡፡ ሰላም የእድገት መሰረት ነው፡፡ የሰው ልጅ ስጋትን አስወግዶ ተረጋግቶ <u>እፎይታ</u> ያለው ህይወት ሊኖር የሚችለው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ከሰላም ውጪ የሚታሰብ ህይወት የተናጋ ፣ የተቃወሰና መጨረሻውም ወድቀት ነው፡፡ ስለሆነም ለአንድ ግለሰብ ወይም ለአንድ ሀገር ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ በሙሉ የኑሮው ዋልታና ማገር ነው፡፡ ለመኖር የሚደረግ እንቅስቃሴ ቀላልም ሆነ ከባድ ከሰላም ውጪ ዕውን ሊሆን አይችልም፡፡ ሰርቶ ለመኖር አግኝቶ ለመደሰት ተወልዶ ለማደግ ተምሮ በእውቀት በልጽጎ ራስን ለመቻልም ሆነ ሀገርን ለመጥቀም የሰላም መኖር ከሁሉ ቀዳሚ ነው፡፡ የሰው ልጅ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሆኖ ተመራምሮ በዕውቀቱ በልጽጎ ችግርንና በሽታን አስወግዶ <u>የተሻለና የተደላደለ</u> ህይወት ለመመስረት የሰላም መኖር የግድ ነው፡፡ በአጠቃላይ በሀገርም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ጤናማ ግንኙነትን ለመፍጠርና ህዝቦች እንዲቀራረቡ በማድረግ ሰላም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ዓለም ከጦርነት ተላቃ የሰላም ቡቃያ እንዲያብብባት የሁሉንም ጥረት ይጠይቃል፡፡ የዓለም ህዝቦችና መንግስታት ሁሉ በአንድ ልብ ለሰላም መነሳት አለባቸው፡፡ እውነተኛ ሰላም ሊገኝ የሚችለው በሰላማዊ መንገድ፣ ችግሮችን በመግባባትና በውይይት በመፍታት ነው፡፡

1. የህይወት ዋስትና ሲል -------------ማለቱ ነው፡፡

A. ግንዛቤ

B. መሰረት

C. እንቅፋት

D. እስትንፋስ

2. የሰላም አለመኖር መጨረሻው ምንድን ነው?

A. ውድቀት

B. ብልጽግና

C. ፍርሀት

D. ሂደት

3. "የተሻለና የተደላደለ" ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው?

A. የተጣደፈ

B. የዘገየ

C. የተመቻቸ

D. የቆየ

4. የሰው ልጅ ስጋትን አስወግዶ እና እፎይታ ያለው ህይወት ሊኖር የሚችለው ሰላም ሲኖር ብቻ ነው ሲል፡-

A. የሰላም ዋጋው ትንሽ ነው፡፡

B. ያለሰላም መኖር ይቻላል፡፡

C. በስጋት መኖር ተገቢ ነው፡፡

D. ሰላም መረጋጋት የሚሰጥ ነው፡፡

5. ምንባቡ የሚያስተላልፈው መልዕክት፡-

A. ሰላም የህይወት ዋስትና ነው፡፡

B. ያለሰላም መኖር ይቻላል፡፡

C. ከሰላም የሚበልጠው ብልጽግና ነው፡፡

D. ያለ ሰላም ነግዶ ማትረፍ ይቻላል፡፡

***መመሪያ ሁለት***፡- ከተራ ቁጥር 6 እስከ 12 ድረስ ለቀረቡት ***ቃላት*** ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

6. ዓለሙ በትምህርቱ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡ ነገር ግን ማጥናት አይወድም፡፡ የተሰመረበት ቃል ምንን ይገልፃል?

A. ማሰሪያ

B. ተሳቢ

C. አያያዥ

D. ግስ

7. "ባይተዋር" ለሚለው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ከሚከተሉት የቱ ነው?

A. ቋሚ

B. ነዋሪ

C. ደምበኛ

D. እንግዳ

8. ሰሞኑን የሰማሁት ወሬ ምንም ረብ የለውም፡፡በሚለው ዓረፍተ ነገር ለተሰመረበት ቃል **ተመሳሳይ** ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

A. የማይሆን

B. ጥቅም

C. የማይስማማ

D. እርባና ቢስ

9. ይፋ ለሚለው ቃል በፍቺ **ተቃራኒ** የሆነው የቱ ነው?

A. ገሀድ

B. የወፈረ

C. ግልጽ

D. ድብቅ

10. ባልደረባ ለሚለው ቃል **ተመሳሳይ** ፍቺ የሆነው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

A. ባለጋራ C. ወንድም

B. አብሮ የሚሰራ D. የሀገር ልጅ

11. ሰጋ የሚለው ቃል ሳልቶ ሲነበብ የሚሰጠው ፍቺ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

A. ያልበሰለ C. ሸበላ

B. መታ D. ቁመና

12. ህዝቡ **በነቂስ** ወጥቶ ሰፈሩን አጸዳ፡፡ በሚለው ዓረፍተ ነገር ከስሩ የተሰመረበት ቃል **ተቃራኒ** ፍቺ የሆነው፡-

A. ሁሉም C. በተናጠል

B. በሙሉ D. በጠቅላላ

***መመሪያ ሶስት***፡-ከተራ ቁጥር 13 እስከ 25 ድረስ **ሰዋሰውን** የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

13. ከሚከተሉት **ትዕዛዛዊ** ዓረፍተ ነገር የሆነው የትኛው ነው?

A. ወደቤት አልሄድም ፡፡ C. አየለ መቼ ትመጣለህ?

B. አየለ ምሳህን ብላ፡፡ D. አየለ ምን በላህ?

14. አልማዝ **ቆቅ** ነች፡፡ የተሰመረበት ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ የሆነው የቱ ነው?

A. ጎበዝ C. ንቁ

B. የወፍ ዝርያ D. ፈሪ

15. "**እርግብ**" ለሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቺ የቱ ነው?

A. የዋህ C. ድሀ

B. ንፉግ D. የወፍ ዝርያ

16. ቀጥሎ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ **በተራ** ዓረፍተነገር የተገለጸው የቱ ነው?

A. ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ወጡ። C. ሰራተኞች ገንዘባቸውን ስለጨረሱ ተቸገሩ።

B. ለማ ቁርሱን በልቶ ወደ ገበያ ሄደ። D. አባቱ በመምጣቱ ደስ አለው።

17. ከሚከተሉት ውስጥ **ውስብስብ** ዓረፍተ ነገር የሆነው የትኛው ነው?

A. አበበ እራሱን ስለ አመመው ወደ ሀኪም ቤት ሄደ። C. ገበሬው ማሳውን አጠረ።

B. ጥበቃው በሩን ዘጋው። D. ሰፈራቸውን በህብረት አጸዱ።

18. ከሚከተሉት **በአሉታዊ** ዓረፍተ ነገር የተጻፈው የቱ ነው?

A. ቁርስህን ብላ። C. ዛሬ ልብሴን አላጥብም።

B. ወደ ትምህርት ቤት ሂድ። D. ከመቀመጫህ ተነስ።

19. ቀጥሎ ከቀረቡት ውስጥ ስህተት ያለበት አጻጻፍ የቱ ነው?

A. የሀይሉ እህት አገባች። C. ረጅሙን ዛፍ ቆረጡት።

B. ይህ ጫማ ተውና ያ አድርግ። D. ሻዩ ውስጥ ብዙ ስኳር አለበት።

20. ረባሹ ተማሪ ከትምህርት ቤት ተባረረ።በሚለው አረፍተ ነገር **የስም ገላጭ** የቱ ነው?

A. ተባረረ C. ከትምህርት ቤት

B. ተማሪ D. ረባሹ

21. ጎበዟ መምህርት <u>**ክፉኛ**</u> ታማለች ፡፡በሚለው ዓረፍተ ነገር የተሰመረበት ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል?

A. ተውሳከ ግስ C. ስም

B. ቅጽል D. መስተዋድድ

22. ተግቶ ያጠና ተማሪ ውጤታማ ይሆናል፡፡በሚለው ዐረፍተ ነገር <u>የግስ ገላጭ</u> የቱ ነው?

A. ተግቶ C. ተማሪ

B. ያጠና D. ውጤታማ

23. "ሀሜሶ ትምህርቱን ጨርሶ እንጀራ ወጣለት፡፡" የሚለው ዓረፍተ ነገር የተጻፈው ከሚከተሉት በየትኛው አጻጻፍ ነው?

A. ምንባብ C. ግጥም

B. ፍካሬያዊ D. ሀረግ

24. ወንድሜ <u>ገና</u> አልመጣም ፡፡የተሰመረበት ቃል ከሚከተሉት የትኛውን ያመለክታል?

A. ሁኔታን አመልካች C. ጊዜን አመልካች

B. ቦታን አመልካች D. ብዛትን አመልካች

25. ሱራፌል ከአዲስ አበባ ዛሬ <u>**ወይም**</u> ነገ ይገባል፡፡ የተሰመረበት ቃል የሚያመለክተው የቱ ነው?

A. አያያዥ C. አነጻጻሪ

B. መስተዋድድ D. ገላጭ

***መመሪያ አራት***፡-ከተራ ቁጥር 26 እስከ 33 ድረስ **የክሂል** ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ይበልጥ ትክክል የሆነውን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

26. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ከሰው መልዕክት መቀበያ መንገድ የሆነው የትኛው ነው?

A. በዝምታ C. በሳቅ

B. ኩርፊያ D. ማዳመጥ

27. አንድ ሰው ለሌላኛው ሰው መረጃ ማስተላለፍ ቢፈልግ በየትኛው ዘዴ መጠቀም አለበት?

A. በማየት C. በመንካት

B. በመጻፍና በመናገር D. በመራመድ

28. አንድን ሀሳብ በተሟላ ሁኔታ ሊያስተላልፍ የሚችል የቃላት ወይም የሀረጋት ቅንጅት ምን ይባላል?

A. ድርሰት C. ዓረፍተነገር

B. ስነቃል D. ግጥም

29. ድምጾችን ስርዓት ባለው መልክ በመደርደር ትርጉም ያለውን መልዕክት ለሰዎች ማስተላለፍ ምን ይባላል?

A. ግንኙነት C. ማዳመጥ

B. መናገር D. ውይይት

30. ----------- ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚያካሂዱትና ሀሳብና ስሜታቸውን የሚገልጹበት ነው፡፡

A. ጭውውት C. ስኬት

B. ግንኙነት D. ጓደኝነት

31. ወተት ከሚለው ቃል ወተታም የሚል ገላጭ ቃል ቢወጣ ሆድ ከሚለው ቃል------ይወጣል፡፡

A. ሆድዬ C. ሆዳም

B. ልባም D. ሆዴን

32. "ችግረኛን መርዳት በህይወት እያለ ነው" ይህ አባባል ምንን ያመለክታል፡፡

A. ችግረኛን መርዳት ሲሞት ነው፡፡ C. ሰው ቢረዳም ባይረዳም ትርጉም የለውም፡፡

B. ሞት ማንንም አይመርጥም፡፡ D. ችግረኛ ከመሞቱ በፊት መረዳት አለበት፡፡

33. ንግግርን እንዲዳብር ከሚያደርጉ አባባሎች አንዱ የሆነው፡-

A. ዝምታ ወርቅ ነው፡፡ C. በለፈለፉ በአፍ ይጠፉ፡፡

B. ከመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል፡፡ D. ዝም አይነቅዝም፡፡

***መመሪያ አምስት***፡-ከተራ ቁጥር 34 እስከ 39 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ***ግጥም*** ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ግጥሙን በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ይበልጥ ትክክል የሆነውን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

"ቆንጆ ኅበዝ ሀብታም አዋቂ ተብሎ፣

ያዳምልጅ በመሬት እንደ አበባ በቅሎ፣

አንድ እንኳን ሳይታይ ከመካከል ተርፎ፣

ሁሉም ወዳቂ ነው እንደ አበባ ረግፎ።"

34. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

A .6 C. 4

B. 5 D. 3

35. የአራተኛው ስንኝ መድረሻ ሀረግ የሚሆነው የቱ ነው?

A .ሁሉም ወዳቂ ነው C. ከመካከል ተርፎ

B. አዋቂ ተብሎ D. እንደ አበባ ረግፎ

36. የሶስተኛው ስንኝ ቤት መምቻው ቃል የሆነው የቱ ነው?

A. ተርፎ C. በቅሎ

B. ተብሎ D. ረግፎ

37. የአንደኛው ስንኝ መነሻ ሀረግ የሆነው የትኛው ነው?

A. ቆንጆ ኅበዝ ሀብታም C. አዋቂ ተብሎ

B. ያዳም ልጅ በመሬት D. ሀብታም አዋቂ

38. ግጥሙ ስንት ሀረጎች አሉት?

A. 6 C. 8

B. 7 D. 9

39. ግጥሙ ስንት መነሻ ሀረጎች አሉት?

A. 1 C. 3

B. 2 D. 4

***መመሪያ* ስድስት**፡-ከተራ ቁጥር 40 እስከ 60 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች **የስነጽሁፍ** ትምህርት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ይበልጥ ትክክል የሆነውን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

40. አንድን ሀሳብ የሚዘረዝሩና የሚያብራሩ ዓረፍተ ነገሮች ያሉት አነስተኛ ጽሁፍ የቱ ነው?

A. ድርሰት C. ምንባብ

B. አንቀጽ D. ቃላት

41. አንድ አንቀጽ በውስጡ ከሚይዘው ነገር አንዱ የቱ ነው?

A. መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር C. ስነቃል

B. ስነ-ጽሁፍ D. መመሪያ

42. ስላለፈው ድርጊት የሚያትት የድርሰት አይነት የቱ ነው?

A. ስዕላዊ ድርሰት C. ተራኪ ድርሰት

B. አከራካሪ ድርሰት D. አመዛዛኝ ድርሰት

43. አስተዋጽኦ መንደፍ የሚያስፈልግበት ዋና ዓላማ ምንድነው?

A. የደራሲውን ችሎታ ለማሳየት C. የሚጻፈውን ጽሁፍ ለማስረዘም

B. ከዋናው ሀሳብ ላለመውጣት D. ከሌሎች ልዩ ለመሆን

44. አከራካሪ የሆኑ ጉዳዮችን በመደገፍም ሆነ በመቃወም የሚጻፍ፤አንባቢን ለማሳመን የሚጥር የድርሰት አይነት ምን ይባላል?

A. ተራኪ ድርሰት C. ስዕላዊ ድርሰት

B.ገላጭ ድርሰት D. አመዛዛኝ ድርሰት

45. ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች የአጭር ልብ-ወለድ ባህሪ **የሆነው** የቱ ነው?

A. ጭብጡ ከአንድ በላይ ነው፡፡ C. መቼቱ ሰፊ ነው፡፡

B. ታሪኩ በተወሰነ ቦታና ጊዜ ይፈጸማል፡፡ D. ከልደት እስከ ሞት ያቀርባል፡፡

46. አጭር ልብ-ወለድንና ረጅም ልብ-ወለድን አንድ የሚያደርጋቸው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

A. ምልልስን ያስተናግዳሉ፡፡ C. በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ይፈጸማሉ፡፡

B. በጥድፊያ ይሞላሉ፡፡ D. በርካታ ግጭቶች ይኖሩታል፡፡

47. ኢ-ልብወለድ ከልብ-ወለድ የሚለየው ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች በየትኛው ነው?

A. የማስዋብና የማጋነን ሁኔታ ተፈላጊነት አላቸው፡፡

B. የልብ ወለድ አላባዊያን ይኖሩታል፡፡

C. በተጨባጭ የተከናወነ፣ የተደረገ ድርጊት ላይ ያተኩራል፡፡

D. በጽሁፉ ውስጥ ቦታ፣ ባለታሪክና ሁኔታ በጸሀፊው ቁጥጥር ስር ናቸው፡፡

48. "ሺ ቢታለብ ያው በገሌ አለች፣ ድመት፡፡" የሚለው ሀሳብ የተገለጸው በየትኛው የዘይቤ አይነት ነው ?

A. ተምሳሌታዊ ዘይቤ

B. ግነት ዘይቤ

C. ተለዋጭ ዘይቤ

D. ሰውኛ ዘይቤ

49. **"ቀልብ ገዛ"** ለሚለው ፈሊጣዊ አባባል ፍቺ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

A. ከውካዋ

B. አስተዋይ ሆነ

C. ተጨነቀ

D. ምግብ ገዛ

50. በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ዝርዝር ነገሮችን ለመለየት የምንጠቀመው ስርዓተ ነጥብ፦

A. አራት ነጥብ

B. ድርብ ሰረዝ

C. ነጠላ ሰረዝ

D. ቃለ አጋኖ

51. በትክክል የተገለጸው ዓረፍተ ነገር የቱ ነው?

A. ምግባር መልካም በትምህርት ቤት ተማሪው አለበት ማሳየት፡፡

B. በትምህርት ቤት አለበት ማሳየት ምግባር መልካም፡፡

C. ማሳየት አለበት በትምህርት ቤት ምግባር መልካም፡፡

D. ተማሪው በትምህርት ቤት መልካም ምግባር ማሳየት አለበት፡፡

52. የአጻጻፍ ስርዓቱን ጠብቆ የተገለጸው የቱ ነው?

A. ተማሪዎች ቢያበሳጩኝም አልጠላቸውም፡፡

B. አልጠላቸውም ቢያበሳጩኝም ተማሪዎች፡፡

C. አልጠላቸውም ተማሪዎች ቢያበሳጩኝም፡፡

D. ቢያበሳጩኝም አልጠላቸውም ተማሪዎች፡፡

53. ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛ አገላለጽ የተጻፈው የትኛው ነው?

A. ሀይለኛ ዝናብ መጥቷል ፤ስለዚህ ወደቤት ቶሎቶሎ እንሂድ፡፡

B. ሀይለኛ ዝናብ መጥቷል ! ስለዚህ ወደቤት ቶሎቶሎ እንሂድ፡፡

C. ሀይለኛ ዝናብ መጥቷል፡ ስለዚህ ወደቤት ቶሎቶሎ እንሂድ፡፡

D. ሀይለኛ ዝናብ መጥቷል? ስለዚህ ቶሎ ቶሎ እንሂድ፡፡

54. ቀጥሎ ከቀረቡት መካከል የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ የቱ ነው?

A. የምናዳምጠውን ሁሉ ማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል ፡፡

B. ማስታወሻ ለመያዝ ብዕርና ደብተር መያዝ አለብን፡፡

C. ማስታወሻ በውይይት መልክ መያዝ አለብን ፡፡

D. ማስታወሻ ለመያዝ መመሪያ አያስፈልግም፡፡

55. ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ስርአተ ነጥቡን ጠብቆ የተጻፈው የቱ ነው?

A. መድሀኒት ከገበያ ሽንኩርት፡ ቡና፡ ድንች፣ ካሮትና ቀይስር ገዝታ መጣች፡፡

B. መድሀኒት ከገበያ ሽንኩርት፣ቡና፣ ድንች፣ ካሮት፤ ቀይስር ገዝታ መጣች፡፡

C. መድሀኒት ከገበያ ሽንኩርት፣ ቡና፡ ድንች፡ ካሮትና ቀይስር ገዝታ መጣች፡፡

D. መድሀኒት ከገበያ ሽንኩርት፣ ቡና፣ ድንች፣ ካሮትና ቀይስር ገዝታ መጣች፡፡

56. በአንድ አንቀጽ ውስጥ የሚገኘውን ሀሳብ አጠቃሎ የያዘና በሱ ዙሪያ ያሉ ሌሎች ዝርዝር ዓረፍተ-ነገሮችን የያዘ የጽሁፍ ክፍል፡-

A. ድርሰት

B. ምዕራፍ

C. ሀይለቃል

D. ልብ-ወለድ

57. በልብወለድ ውስጥ በምክንያትና በውጤት የተሳሰረ የድርጊቶች ቅደም ተከተል የሆነው የቱ ነው?

A. ትልም

B. ታሪክ

C. መቼት

D. ውጤት

58. ሆድ ለባሰው -----------ምሳሌያዊ አነጋገሩን ሊያሟላ የሚችለው ሀሳብ የቱ ነው?

A. ቀለብ አትስጠው

B. ፈጥነህ አጉርሰው

C. ማጭድ አታውሰው

D. ምንም አትንገረው

59. "ወይ ጉድ---" የሰራችሁት ስራ በጣም ይገርመኛል፡፡ በባዶ ቦታ የሚገባው ስርዓተ ነጥብ፡-

A. ነጠላ ሰረዝ

B. የጥያቄ ምልክት

C. ትዕምርተ ስላቅ

D. የቃለ አጋኖ ምልክት

60. ከዚህ በታች ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቀው የተጻፉት ዓረፍተ ነገሮች በትክክለኛው የሀሳብ ቅደም ተከተል ሲጻፍ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

1. ከጊዜ ውጪ የተደረገና ሊደረግ የሚችል ነገር የለም።
2. ይሁንና ይህ ያልገባቸው ብዙ ሰዎች በጊዜ እየተቀደሙ የቆሙበት ቀርተዋል።
3. ስለዚህ የጊዜ አጠቃቀም ተገቢ ትኩረት ይጠይቃል።
4. ድርጊት ሁሉ የሚከናወነው በጊዜ ተወስኖ ነው።

A. 3፣4፣1፣2

B. 4፣1፣3፣2

C. 4፣2፣3፣1

D. 2፣3፣1፣4

.

# አባሪ ሁለት

## የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና

**የጥያቄብዛት፡- 60**

**የተሰጠው ሰዓት፡- 60 ደቂቃ**

**ሰኔ 2011/2019**

**ክፍል አንድ**

**የቃላት ጥያቄዎች**

***መመሪያ አንድ፡-*** ከተራ ቁጥር 1-10 ለተሰጡት ቃላት ነክ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥበመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

1. ካለፈው የሙከራ ጥያቄ 22ኛው **ጠጣር** በመሆኑ ብዙ ተማሪዎች አይሰሩትም፡፡

   የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ---------------ነው፡፡

   A. ከባድ  C. ረጃጅም

   B. ገራገር  D. ቀላል

2. የደን **መጨፍጨፉ** ለአየር ንብረት መዛባት ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ለተሰመረበት ቃል **ተቃራኒ** ሊሆን የሚችል ቃል የቱ ነው?

   A. መቁረጥ  C. መንቀል

   B. ማቃጠል  D. መትከል

3. ከሚከተሉት ቃላት መካከል **ቅጽል** የሆነው የትኛው ነው?

A. ቶሎ C. ትንሽ

B. በላ D. እንደ

4. በመድረሻው ላይ “---ነት” የሚል ቅጥያ በመውሰድ ሊመሰረት የሚችለው የትኛው ቃል ነው?

A. መንገድ C. ሀገር

B. ማህበር D. ልጅ

5. በመድረሻ ላይ “ኣዊ” የሚል ቅጥያ በመውሰድ ሊመሰረት የሚችለው የትኛው ቃል ነው?

A. ብርድ C. ትክክል

B. ባህል D. ሆድ

6. “ልጅነት” በሚለው ቃል ላይ - ኣቸው የሚለው ቅጥያ ሲገባ የሚገኘው ቃል የትኛው ነው?

A. ልጃቸው C. ልጅነታቸው

B. ልጅነቶቻቸው D. ልጆቻቸው

7. “አስተማሪዎችን” የሚለው ቃል በዋና ቃልና በቅጥያ ተተንትኖ ሲጻፍ የትኛው ትክክል ነው?

A. አስ-ተማሪ-ዎች-ን C. አስተማሪ-ዎች-ን

B. አስተማሪ- ዎችን D. አስተማሪዎች-ን

8. “ሰበረ” ብሎ መስበር ካለ ገደለ ብሎ ------------ ይላል፡፡

A. አስገደለ C. መግደያ

B. መግደል D. ግድያ

9. ቤት ከሚለው ቃል ጋር በመቀናጀት ድርብ (ጥምር) ቃል ሊመሰረት የሚችለው የቱ ነው?

A. ሀገር
C. ሰባራ
B. ስውር
D. መጽሀፍ

10. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በፊደል ተራ ቅደም ተከተል መጀመሪያ ሊሆን የሚችለው የትኛው ቃል ነው?

A. ሌባ
C. ቃጭል
B. ባትሪ
D. መብራት

## ክፍል ሁለት

## ሰዋስውዋዊ ጥያቄዎች

***መመሪያ ሁለት፡-*** ከተራ ቁጥር 11-16 ለቀረቡት ሰዋስዋዊ ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

11.ለሰዎች ወይም ለነገሮች መጠሪያ (ስያሜ) በመሆን የሚያገለግል የቃል ክፍል--------በመባል ይታወቃል፡፡

A. ቅጽል
C. ስም
B. ግስ
D. መስተዋድድ

12.አቶ ዘለቀ ታታሪ ገበሬ ናቸው፡፡ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ መሙያ ሆኖ ያገለገለው ስማዊ ሀረግ --------- ነው፡፡

A. ታታሪ ገበሬ
C. ታታሪ
B. አቶ ዘለቀ
D. ገበሬ ናቸው

13. "አለሙ ምሳን በላ፡፡" የሚለው አረፍተ ነገር ወደ አሉታዊ አረፍተ ነገር ሲቀየር ------------ ይሆናል፡፡

A. አለሙ ምስውን ይብላ፡፡
C. አለሙ ምሳውን አልበላም፡፡
B. አለሙ ምሳውን በልቷል፡፡
D. አለሙ ምሳውን መቼ በላ?

14. እነዚያ የታቦርና የአላሙራ ተራሮች ለሀዋሳ ከተማ ሞገስ ሆነዋታል፡፡ በዚህ አረፍተ ነገር

ውስጥ ጠቋሚ መስተኣምሩ ማነው?

A. ሞገስ

B. እነዚያ

C. ተራሮች

D. ሀዋሳ ከተማ

15. ቁርሱን ስላልበላ ----------------- ፡፡ ለባዶ ቦታው ተስማሚ ሊሆን የሚችለው ውጤት የትኛው ነው?

A. አዙሮት ወደቀ

B. በርትቶ አጠና

C. ፊቱ በራ

D. ጠነከረ

16. "ስራዬን ባልጨርስም መሄዴ የማይቀር ነው፡፡" የሚለው ሀሳብ በሌላ አባባል ሲገለጽ የትኛውን ይመስላል?

A. ስራዬ ካልተጠናቀቀ መሄድ አልችልም፡፡

B. የመሄዴ ጉዳይ የሚወሰነው ስራዬ ሲጠናቀቅ ነው፡፡

C. ስራዬን ስላጠናቀቅሁ መሄድ አለብኝ፡፡

D. የስራዬ አለመጠናቀቅ ከመሄድ አያግደኝም፡፡

## ክፍል ሶስት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

***መመሪያ ሶስት፡-*** ከተራ ቁጥር 17 እስከ 30 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

### ምንባብ

አቶቴ ጥሩ ሳር የሚበቅልበትንመስክና ውሃ የሚፈስበትን አመቺ ቦታ መርጣ ላም ታረባለች፡፡ ሰራተኞቿ ለላሞቹ መኖ እንደልብ ስለሚያቀርቡላቸው ጋኖቹ ጢም ብለው በወተት ይላሉ፡፡

ከሚታለበው ወተት ገሚሱ ትኩሱን ሲሸጥ የቀረው በእቃ ተቀምጦ እየረጋ ይናጣል፡፡ የረጋውን ወተት የሚንጥ ሌላ ሰው ተቀጥሮ ቀኑን ሙሉ ሲንጥ ይውላል፡፡ ያ ሁሉ የተትረፈረፈ ወተት ምንም ሳይቀር ወደ ማጠራቀሚያው ይጨመራል፡፡ ባዶ <u>ሆዳቸውን</u> ለስራ የምታሰማራቸው አላቢዎች ከትኩሱ ወይ ከእርጎው ቢቀር ከተናጠው እንኳን ለመቅመስ ስላልተፈቀደላቸው <u>**ዘወትር**</u> እንደጓጉ ይኖራሉ፡፡ ተደብቆ መጠጣት ቢቻል ኖሮ አላቢዋም የትኩስ ወተት አረፋ ሲያውዳት ሁለቴ <u>**ጎንጨት**</u> ማድረጓ የማይቀር ነበር፡፡ ናጩም ቅቤውን ካወጣ በኋላ ከአሬራው ሁሌም ባይሆን አልፎ አልፎ አንድ መጥለቂያ ያህል ቢጠጣ ምን ያህል በተደሰተ! ታዲያ በየት በኩል ሲታለብ ቆሞ የሚጠብቅ ሰው አቁማለች፡፡ ጠባቂው ድንገት ከነሱ ጋር ተማክሮ ወተት ይጠጣል ብላ እራሷም ቁጥጥር ታደርጋለች፡፡ ወተት ታልቦ ማለቢያው ሲሞላ ጠባቂው እየተከተላት አላቢዋ ወስዳ ከትልቅ <u>**እንስራ**</u> ውስጥ ትገለብጣለች፡፡ ታልቦ እንዳበቃም አላቢዋ ማለቢያውን አጥቦ ወደምታጥንበት ቤት ትወስደዋለች፡፡ አቴቶም ቅቤ የሚያወጣበትን ጊዜ በግምት ስለምታውቀው ከች ትላለች፡፡ ቅቤው በአንድ እቃ ይወጣና አሬራውን በሌላ እቃ አስጨምራ "በል መናጫውን በሚገባ አጥበህ በወይራ እጠነው" የሚል ትእዛዝ ለናጩ አስተላልፋ ትሄዳለች፡፡

**ምንጭ፡- (ወጋየሁ ተበጀ፣ ባለወተት ገጽ 86-87 ለፈተና እንዲመች በጥቂቱ የተሻሻለ)**

17. "--- መኖ---" ለሚለው ቃል አቻዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?
    A. ወተት
    B. ጥጃ
    C. እረኛ
    D. የከብቶች ቀለብ
18. ምንባቡ ስንት አንቀጽ አለው?
    A. አራት
    B. ሶስት
    C. አንድ
    D. ሁለት
19. በምንባቡ መሰረት የወተት ውጤት ቅደም ተከተላዊ ሂደት የሚሆነው የቱ ነው?
    A. ማርጋት፣ ማለብ፣ ቅቤውን ማውጣት፣መናጥ
    B. ማለብ፣ ማርጋት፣ መናጥ፣ ቅቤ ማውጣት
    C. ቅቤማውጣት፣ መናጥ፣ ማለብ፣ ማርጋት

D. መናጥ፣ ቅቤ ማውጣት፣ ማለብ፣ ማርጋት

20. በምንባቡ ውስጥየተጠቀሰችው ሴት ባህሪ ምን አይነት ነው?

A. ንፉግ C. ሩህሩህ

B. ለጋስ D. አዛኝ

21 አቶቴ ወተት ሲታለብ ጠባቂ የምታቆመው ለምንድነው?

A. ወተት እንዳይደፋ C. ሰራተኞቹ እንዳይደክማቸው

B. ሰራተኞቹ ወተት እንዳይጠጡ D. ሰራተኞቹን ለማገዝ

22. ከባለ ወተቷ ሴት ተግባር ምን መታዘብ ይቻላል?

A. ሰራተኞችን አለማመን ተገቢ መሆኑን

B. ለሰራተኞች ነጻነት መስጠት ተገቢ መሆኑን

C. ሰራተኞችን በአግባቡ የመያዝ ችግር እንዳለባት

D. ስራን ከፋፍሎ መስጠት ተገቢ መሆኑን

23. በምንባቡ መሰረት "... ከወተቱ ሁለቴ ጎንጨት ማድረጓ ..." በሚለው ሃሳብ ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ የትኛው ነው?

A. ፉት C. ገመጥ

B. ጎረሰ D.ጭልፍ

24. "ዘወትር" ለሚለው ቃል ተቃራኒ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

A. እለት ከእለት C. በየቀኑ

B. ሁልጊዜ

D. አልፎ አልፎ

25. እንደ ምንባቡ ሀሳብ የሰራተኞቹ የዘወትር ጉጉት ምንድነው?

A. እረፍት ማድረግ

C. ከሚያልቡት ወተት መጠጣት

B. ጠግቦ መብላት

D. ሀብታም መሆን

26. … አላቢዎቹ **ዘወትር እንደጓጉ ይኖራሉ**፡፡ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ግስ የሆነው ቃል የቱ ነው?

A. አላቢዎቹ

C. ይኖራሉ

B. ዘወትር

D. እንደጓጉ

27. ምንባቡ የተጻፈበት የድርሰት አይነት --------------- ነው?

A. በተራኪ

C. በአመዛዛኝ

B. በስእላዊ

D. በገላጭ

28. "**ወተቱን በትልቁ እንስራ ትገለብጣለች**፡፡" በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የተሰመረበት ቃል ጠብቆ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጉም ------------ ነው፡፡

A. እናቅድ

C. እናውራ

B. እንመዝን

D. እንተግብር

29. አቶቱ ከሰራተኞቿ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራት ምን ማድረግ ይኖርበታል?

A. ቅጥጥሯን ማጥበቅ

C. ስራዋን እራሷ መስራት

B. ሰራተኞቿን በፍቅር መያዝ

D. ብዙ ተቆጣጣሪ መመደብ

30. **“ሆዳቸውን”** የሚለው ቃል በስተመድረሻው ስንት ጥገኛ ምእላዶችን ይዟል?

A. ሁለት C. አራት

B. ሶስት D. አምስት

***ምእራፍ አራት***

***የጽህፈት ጥያቄዎች***

***መመሪያ አራት፡-*** ከተራ ቁጥር 31 እስከ 44 ለቀረቡት ጽህፈትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ።

31. የሌላን ሰው ሀሳብ፣ ንግግር ወይም ጽሁፍ እንዳለ ወስደን በጽሁፍ ውስጥ ለመጠቀም የሚያገለግለን ምን አይነት ነጥብ ነው?

A. ነጠላ ሰረዝ C. ቃለ አጋኖ

B. ትእምርተ ስላቅ D. ትእምርተ ጥቅስ

32. ፋጡማ አስናቀ ደያሶ እና ጸሀይ አብረው ወደ ትም/ቤት ሄዱ። በስሞች መካከል የሚገባው ስርአተ ነጥብ ምንድነው?

A. “ ” C. ፣

B. ! D. ?

33. “የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልላዊ መንግስት” የሚለው ቃል በምህጻረ ቃል ሲጻፍ የትኛው ትክክል ነው?

A. የ.ደ.ብ.ብ.ህ.ክ.መ C. የደ.ብ.ብ.ህ.ክ.መ

B. ደ.ብ.ብ.ህ.ክ.መ D. ደ.ብ.ህ.ክ.መ

34. በትክክለኛው የስርአተ ነጥብ አገባብ የተጻፈው የትኛው ነው?

A. የቤት ስራህን እስካሁን ለምን አልሰራህም።

B. የቤት ስራህን እስካሁን ለምን አልሰራህም?

C. የቤት ስራህን እስካሁን ለምን? አልሰራህም?

D. የቤት ስራህን እስካሁን "ለምን አልሰራህም?"

35. ክፍላችን በደንብ ስለጸዳ ተመልካችን ይማርካል። ---------- ብዙ ነገሮች ይጎድሉታል። ተገቢው አያያዥ ቃል የትኛው ነው?

A. እና C. ስለሆነም

B. ወይም D. ይሁን እንጂ

36. የፈተና ጊዜ ተቃርቧል። ------------ ተማሪዎች ተግተው ማጥናት ይኖርባቸዋል። ትክክለኛው አያያዥ ቃል የትኛው ነው?

A. ስለዚህ C. ወይም

B. ሆኖም D. ነገር ግን

37. በትክክለኛው የአጻጻፍ ስርአት የተገለጸው አረፍተ ነገር የትናው ነው?

A. በጎ በሰራው ስራ አብደላ ተደነቀ። C. አብደላ በሰራው በጎ ስራ ተደበቀ።

B. ተደነቀ አብደላ በሰራው በጎ ስራ። D. በጎ ስራ በሰራው አብደላ ተደነቀ።

38. የቡና አፈላል ሂደትን በቅደም ተከተል የሚገልጸው የትኛው ነው?

A. ይታጠባል፣ይወቀጣል፣ይቆላል ይፈላል። C. ይቆላል፣ይወቀጣል፣ይፈላል፣ይታጠባል።

B. ይፈላል፣ይወቀጣል፣ይቆላል፣ይታጠባል። D. ይታጠባል፣ይቆላል፣ይወቀጣል፣ይፈላል።

39. ቀጥሎ ከቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ትክክለኛውን የአረፍተ ነገር አመሰራረት ስርአት የተከተለው የቱ ነው?

A. ጊዜ ይፈልጋል ተግባር ማንኛውም C. ይፈልጋል ማንኛውም ተግባር ጊዜ

B. ማንኛውም ተግባር ጊዜ ይፈልጋል። D. ማንኛውም ይፈልጋል ጊዜ ተግባር

40. ቀጥሎ ተዘበራርቀው የተጻፉ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል። በቅደም ተከተል ቢቀመጡ ትክክል የሚሆን የቱ ነው?

1/ በ1982 ዓ.ም በበረራ አስተናጋጅነት ሰለጠኑ።

2/ ወ/ሮ እሌኒ ታደሰ ግንቦት 24/1963 ዓ.ም ተወለዱ።

3/ አውሮፕላን አብራሪ የመሆን ዝንባሌ አደረባቸው።

4/ በ1992 ዓ/ም አብራሪ ለመሆን ወደ ማሰልጠኛ ገቡ።

A. 2፣ 1፣ 3፣ 4 C. 4፣ 3፣ 2፣ 1

B. 1፣ 2፣ 3፣ 4 D. 2፣ 1፣ 4፣ 3

41. ከሚከተሉት መካከል የግለሰብን ህይወት ታሪክ ስንጽፍ የግድ ሆኖ የማያስፈልገን የቱ

ነው?

A. ስለ ግለሰቡ/ቧ/ መረጃ መሰብሰብ፡፡ C. የግለሰቡ/ቧን የግል ሚስጥር መጥቀስ፡፡

B. ማስረጃውን በቅደም ተከተል ማደራጀት፡፡ D. ስለ አስተዳደጓ/ጉ ማተት፡፡

42. በሁለት ቡድኖች መካከል ዳኛ በመሰየም የሚካሄድ ስርአታዊ ሙግት -------- ይባላል፡፡

A. ውይይት C. ጭውውት

B. ክርክር D. ጭቅጭቅ

43. ከሚከተሉት አንዱ በክርክር ወቅት ተገቢ <u>**አይደለም**</u>፡፡

A. ተራን ጠብቆ መናገር C. የዳኛውን ውሳኔ አለመቀበል

B. የመከራከሪያ ርእስን ማወቅ D. ማስታወሻ መያዝ

44. ስለ ቃላዊ ግጥም ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. የሚተላለፍበት መንገድ በቃል ነው፡፡ C. በጽሁፍ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

B. ደራሲው ተለይቶ ይታወቃል፡፡ D. መተላለፊያው በጽሁፍ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## የግጥም ጥያቄዎች

***መመሪያ አምስት፡-*** ከተራ ቁጥር 45 እስከ 51 የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

ንብረት እንዳይወድም ህዝብ እንዳይጎዳ፣

ሹፌር ተጠንቅቆ በስርአት ተነዳ፣

ይህም ሀገር መውደድ መሆኑን ይረዳ፡፡

ዳኛ እውነት ሳይሸጥ ህግን ካስከበረ፣

መምህሩ ሳይታክት ከልብ ካስተማረ፣

ደራሲው በብእሩ ሀቅን ካበሰረ፣

ይህ ነው ሀገር መውደድ እጅግ የከበረ፡፡

**(ከግል ማስታወሻ የተወሰደ)**

45. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?

A. አምስት
C. ስምንት
B. ሰባት
D. አስራ አራት

46. የስንኝ ሶስት መነሻ ሀረግ ምን የሚለው ነው?

A. ይህም ሀገር መውደድ
C. ሀገር መውደድ መሆኑን
B. ይህም ሀገር
D. መሆኑን ይረዳ

47. ግጥሙ በጠቅላላው ስንት የመድረሻ ሀረጎች አሉት?

A. ስምንት
C. አስራ ሶስት
B. ሰባት
D. አስራ አራት

48. “ሳይታክት” ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ------------------- ነው፡፡

A. ሳይደሰት C. ሳይሰለች

B. ሳይበሳጭ D. ሳይዝናና

49. በግትሙ ውስጥ ስንት የቤት መድፊያ ቃላት ይገኛሉ?

A. ሁለት C. አራት

B. ሶስት D. አምስት

50. “ዳኛ እውነት ሳይሸጥ ህግን ካስከበረ” በሚለው ስንኝ ውስጥ የመነሻ ሀረጉ ሀሳብ በሌላ ተመሳሳይ ሀሳብ ቢተካ የበለጠ ተስማሚው አማራጭ የትኛው ነው?

A. ዳኛ እያዳላ C. ዳኛ እያዘነ

B. ዳኛ ሀቅን ይዞ D. ዳኛ ፊት እያየ

51. የግጥሙ መልእክት ምንድን ነው?

A. ሀገርን መውደድ የተወሰኑ ሰዎች ኃላፊነት ነው፡፡

B. ሀገር መውደድ በቃል ብቻ የሚገለጽ ነው፡፡

C. ሀገር መውደድ የመምህራን ብቻ ድርሻ ነው፡፡


D. እያንዳንዱ ሰው ሙያውን አክብሮ ከሰራ ሀገሩን ወዷል ማለት ነው፡፡

**መማሪያ ስድስት**

**ግራፍን የሚመለከቱ ጥያቄዎች**

**መመሪያ ስድስት፡-** የሚከተለው ግራፍ ከ2004 ዓ/ም እስከ 2008 ዓ/ም ድረስ የአይን ህሙማን ህጻናትን ብዛት የሚያሳይ ሀሳባዊ ግራፍ ነው፡፡ ግራፉን መሰረት በማድረግ ከተራ ቁጥር 52 እስከ 55 ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

**የአይን ህሙማንን ብዛት የሚያሳይ**




52. ከ2004 ዓ/ም እስከ 2008 ዓ/ም ባሉት አመታት የታከሙ ህጻናት ብዛት ምን ያህል ነው?

A. 122 C. 142

B. 134 D. 156

53. በቁጥር ትንሽ ህጻናት የታከሙት በየትኛው አመተ ምህረት ነው?

A. በ2008 ዓ/ም
C. በ2006 ዓ/ም
B. በ2007 ዓ/ም
D. በ2005 ዓ/ም

54. በ2007 ዓ/ም የታከሙት ህሙማን በ2008 ዓ/ም ከታመሙት ህሙማን በምን ያህል ቁጥር ይበልጣል?

A. 10
C. 14
B. 13
D. 15

55. ከፍተኛ ህሙማን በታከሙበት አመተ ምህረት እና ዝቅተኛ ህሙማን በታከሙበት አመተ ምህረት መካከል ያለው የህሙማን ቁጥር ልዩነት ስንት ነው?

A. 28
C. 20
B. 24
D. 18

### መመሪያ ሰባት

### ቃላዊ ክሂሎችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

***መመሪያ ሰባት፡-*** ከተራ ቁጥር 56 እስከ 60 ለቀረቡት የሀሳብ ልውውጥና ስነቃላዊ ጥያቄዎች መልሶቻቸውን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡

56. ገሊላ፡- ራሴን በጣም አሞኛል ምን ባደርግ ይሻለኛል?

አልታሞ፡- --------------------------- ፡፡ ለባዶ ቦታው ተገቢ ምላሽ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. በጣም ደስ ይላል C. ችግር የለውም

B. ወደ ትምህርት ቤት ሂጂ D. ለሀኪም አማክሪ

57. አቶ አባይነህ፡- እዚህ ቤት እንኳን አደረሳችሁ!

ወ/ሮ ጣይቱ፡- -------------------------- ። ለባዶ ቦታው ተገቢ ምላሽ የሚሆነው የቱ ነው?

A. እንኳን አብሮ አደረሰን! C. እግዚአብሄር ይስጥልኝ!

B. እንኳን አብሮ ደስ አለን! D. በአምላካችሁ!

58. ከስነቃል አይነቶች መካከል በጠያቂና በተጠያቂ የሚፈጸም ክንውን ምን አይነት ስነቃል ነው?

A. ፉከራ C. ተረት

B. እንቆቅልሽ D. ሙሾ

59. "የኔማ ጌታ የሰጠኝ ሙክት

አንድ አመት ሞላኝ እሱን ሳነክት" ይህ ቃላዊ ግጥም በምን ጊዜ የሚገጠም ነው?

A. የሰርግ B. በሙሾ C. በሆያሆዬ D. በስራ

60. "ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ፣

የልጅነት አይኔ ------------፡፡ ጅምሩን ቃላዊ ግጥም ሊያሟላ የሚችል ሀረግ የትኛው ነው?

A. ተጨናብሶ ቀረ B. ቀረ ተጨማዶ C. እንባ እያፈሰሰ D. ሟሟ እንደበረዶ

# አባሪ ሶስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

**በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ ለፈተናዎች ዝግጅት ክፍል ሀላፊ የቀረበ ቃለ መጠይቅ**

ይህ ጥናት በ2010 ዓ.ም እና በ2011 ዓ.ም በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ተዘጋጅተው በቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ እና የይዘት ተገቢነት ይፈትሻል፡፡ በመሆኑም ይህ ቃለ መጠይቅ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ በመሆኑ እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ለሚጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ ይሰጡ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ፡፡

1. በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛ ቋንቋን እንደአፍ መፍቻ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ክልላዊ ፈተናዎች መሰረት የሚያደርጉት የትምህርት መሳሪያ ምንድን ነው?
2. ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የክልላዊ ፈተናዎች ይዘቶች እንዴት ይመረጣሉ?
3. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና አዘጋጆች እንዴት ይመረጣሉ?
4. ፈተና አዘጋጆች ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲያዘጋጁ ይደረጋል?
5. የፈተና አዘጋጆች የፈተና አዘገጃጀትን በተመለከተ ስልጠና ይወስዳሉ? ፈተናዎቹን ሲያዘጋጁስ የሚከተሏቸው መመሪያዎች አሉ?

6. የፈተና አዘጋጆች ያወጧቸው ፈተናዎች በባለሙያዎች ይገመገማሉ?
7. በየአመቱ የሚሰጡ ክልላዊ ፈተናዎች በተለያዩ አካላት ተገምግመው ግብረ መልስ ታገኛላችሁ? እናንተስ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ?

- ስለክልላዊ ፈተናዎች አዘገጃጀት ጨማሪ አስተያየት ካለዎት?

ስለትብብርዎ በድጋሜ አመሰግናለሁ!